# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

82ኛ ዓመት ቁጥር 083 ኅዳር 23 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72

ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18

ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ


# ከ70 ሺ ሜትሪክ ቶን

## በላይ ምግብና አልሚ ምግብ ወደ ትግራይ ክልል መንጓዙን ኮሚሽኑ አስታወቀ

- ከ460 ሺ. ሊትር በላይ ነዳጅም ተልኳል

**አስቴር ኤልያስ**



ፎቶ - አሸናፊ ጉደታ

አምባሳደር ሽፈራው ተክለማርያም (ዶ/ር)

አዲስ አበባ፡- ከ70 ሺ. ሜትሪክ ቶን በላይ ሰብዓዊ ድጋፍ በእህል እና በአልሚ ምግብ ወደ ትግራይ ክልል መተላለፉን የአደጋ ስጋትና ስራ አመራር ኮሚሽን ኮሚሽነር አምባሳደር ሽፈራው ተክለማርያም (ዶ/ር) አስታወቁ። በመንግስት መሪነት እየተከናወነ ያለው ሰብዓዊ ድጋፉ አጋር ድርጅቶች በአጋርነት እየሰሩ ያለው ተግባር እጅግ በጣም አበረታች መሆኑን ገልጸዋል።

አምባሳደር ሽፈራው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ ከሰላም ስምምነቱ ወዲህ ባለው ጊዜ ብቻ ወደትግራይ ክልል ከተላከው ሰብአዊ ድጋፍ ውስጥ 13 ነጥብ 6 ሺ. ሜትሪክ ቶን እህልና አልሚ ምግብ በመንግስት የተደረገ ነው። ቀሪው ደግሞ በአጋር ተቋማት ተሸፍኗል።

ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሌላው ሲተላለፍ የቆየው የህክምና መድሃኒት እና መገልገያ እቃ ነው ያሉት አምባሳደሩ፣ በዚህም ረገድ ከ800 ሜትሪክ ቶን በላይ ለማስተላለፍ ተችሏል ብለዋል። በሌላ በኩል እጅግ በጣም ለስራው ያስፈልጋል የሚባለው ነዳጅ ሲሆን፣ ይህም ከ460 ሺ. ሊትር

ከ70 ሺ ሜትሪክ ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# ከሱዳን ግዛት በመነሳት በኢትዮጵያ ላይ ጥቃት ለመፈፀም የሚሞክሩ አካላትን ካርቱም አትታገስም

- ጀኔራል አብዱልፈታህ አልቡርሃን

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- ከሱዳን ግዛት በመነሳት በኢትዮጵያ ላይ ጥቃት ለመፈፀም የሚሞክሩ አካላትን ካርቱም አትታገስም ሲሉ የሱዳን ሉዓላዊ የሽግግር ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ጄነራል አብዱልፈታህ አልቡርሃን ተናገሩ፡፡

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን ከሱዳን ሉዓላዊ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ጄነራል አብዱልፈታህ አልቡርሃን ጋር በካርቱም ተወያይተዋል፡፡

በውይይታቸውም በሀገራቱ የሁለትዮሽና አካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ ውጤታማ ምክክር ማድረጋቸውን የኢፌዴሪ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታውቋል።

ኢትዮጵያና ሱዳን በሁለትዮሽና አካባቢያዊ ጉዳዮች ላይ ያላቸው ትብብር እንዲጎለብት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ተቀራርበው ለመስራት መስማማታቸውን ከሚኒስቴሩ ያገኘነው መረጃ ያመላክታል፡፡

ጄነራል አብዱልፈታህ አልቡርሃን በኢትዮጵያ መንግስትና በሕወሓት መካከል የሰላም ስምምነት በመፈረሙ መደሰታቸውን ገልፀው፤ ሀገራቸው ለስምምነቱ አፈፃፀም ሙሉ ድጋፍ እንደምታደርግ አስታውቀዋል።

የሰላም ስምምነቱን ተግባራዊነት የሚያደናቅፉ እንደዚሁም ከሱዳን ግዛት በመነሳት በኢትዮጵያ ላይ

ከሱዳን ግዛት ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



አቶ ደመቀ መኮንን ከሱዳኑ ሉአላዊ ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ጄነራል አብዱልፈታህ አልቡርሃን ጋር ተወያይተዋል

በኢፌዴሪ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት
FDRE Government Communication Service

# የትግራይ ታጣቂዎች ትጥቅ የሚፈቱበትን ዕቅድ የሚያዘጋጀው የባለሙያዎች የጋራ ኮሚቴ ሽሬ ላይ እየመከረ ነው

- የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የትግራይ ታጣቂዎች ትጥቅ የሚፈቱበትን ዝርዝር ዕቅድ የሚያዘጋጀው የባለሙያዎች የጋራ ኮሚቴ ሽሬ ላይ እየመከረ መሆኑን የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አስታወቀ።

በፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት መሠረት ሕወሓት ትጥቅ የሚፈታበትን ዝርዝር ዕቅድ የሚያዘጋጀው

የትግራይ ታጣቂዎች ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል



ፎቶ፡ ፀሐይ ንጉሤ

ዶክተር በለጠ ሞላ

# ጉባዔው ከሁሉም ዓለም ጥግ በመጡ እንግዶች ተሳትፎ መካሄዱ ለኢትዮጵያ ታላቅ ድል ነው

**ዳግማዊት ግርማ**

አዲስ አበባ፡- 17ኛው ዓለም አቀፍ የበይነመረብ አስተዳደር ጉባዔ ከሁሉም የዓለም ጥግ በመጡ እንግዶች ተሳትፎ መካሄድ መቻሉ ለኢትዮጵያ ታላቅ ድል ነው ሲሉ የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትሩ ዶክተር በለጠ ሞላ ገለጹ፡፡

ዶክተር በለጠ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት

ጉባዔው ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል


አዳማ ቆርቆሮ ፋብሪካ
ADAMA STEEL FACTORY




0940 505050/0940 606060/0940 909090/0940 808080/0920 656565


ጉባኤው አፍሪካ የበይነ መረብ ተደራሽነትን በማስፋት የኢኮኖሚ እድገትን ለማስመዝገብ ትልቅ ግብዓት ያገኘችበት ነው

- ተሳታፊዎች

ገጽ 3

# በአፍሪካ ህብረት መሪነት የተጀመረው የሰላም ጥረት ተጠናክሮ እንዲቀጥል አንቶኒዮ ጉተሬዝ አሳሰቡ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ በአፍሪካ ህብረት መሪነት የተጀመረው ሰላምን የማምጣት ጥረት ተጠናክሮ ሊቀጥል እንደሚገባ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ጸሃፊ አንቶኒዮ ጉተሬዝ አሳሰቡ።

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሃፊ አንቶኒዮ ጉተሬዝ ትናንት በአዲስ አበባ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ በአፍሪካ ህብረት መሪነት የተጀመረው ሰላምን የማምጣት ጥረት ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል።

የተደረገው ስምምነት ተፈጻሚነትን በተመለከተም በሁለቱ ወገኖች ወታደራዊ አመራሮች የተጀመረው ንግግር ተስፋ ሰጭ መሆኑን ዋና ጸሃፊው ገልጸዋል።

ህገመንግስታዊ ባልሆነ መልኩ የሚደረጉ የመንግስት መቀየር ሙከራዎች ተቀባይነት እንደሌላቸውም የገለጹት አንቶኒዮ ጉተሬዝ ፤ የአፍሪካ አህጉር ያላትን የመልማት አቅም በመጠቀም ልትለማ እንደሚገባትም አስገንዝበዋል።



አንቶኒዮ ጉተሬዝ እና ሙሳ ፋኪ በጋራ መግለጫ ሰጥተዋል

የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሃፊ አንቶኒዮ ጉተሬዝ እና የአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን ሊቀ መንበር ሙሳ ፋኪ ማሃመት ትናንት መግለጫውን የሰጡት የተባበሩት መንግስታት ድርጅት እና የአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን የሰብዓዊ መብትን በተመለከተ በጋራ በሚያካሂዱት ስብሰባ መክፈቻ ላይ ነው።

ስብሰባው በዋናነት በአፍሪካ ሀገራት ላይ ባለው የሰብዓዊ መብት እና የአየር ንብረት ለውጥ ላይ የሚያተኩር መሆኑ ተገልጿል።

ሙሳ ፋኪ ማሃመት በበኩላቸው፤ የአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን ለተጀመረው የሰላም ስምምነት አስፈላጊውን ድጋፍ ሁሉ እንደሚያደርግ አረጋግጠዋል ሲል ኤፍቢሲ ዘግቧል።

በተመሳሳይ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶክተር) ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት ዋና ፀሃፊ አንቶኒዮ ጉተሬዝ እና ከአፍሪካ ህብረት ኮሚሽን ሊቀ መንበር ሙሳ ፋኪ ማሃመት ጋር ትናንት በጽህፈት ቤታቸው ተወያይተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ከስራ ኃላፊዎቹ ጋር በበርካታ ጉዳዮች ላይ ውጤታማ ምክክር ማድረጋቸውንም በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው አስፍረዋል። ትብብራችን እንደሚጠናከር አልጠራጠርም ሲሉም አረጋግጠዋል።



# የአደንዛዥ ዕጽ ተጠቂነት በፍጥነት እየተስፋፋ ነው

**ቤዛ እሸቱ**

ድሬዳዋ፡- የአደንዛዥ ዕጽ ተጠቂነት በሀገራችን በፍጥነት እየተስፋፋ የመጣ ችግር መሆኑን የሴቶችና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ። የአፍሪካ ወጣቶች ወር የማጠቃለያ መድረክ በድሬዳዋ ከተማ ተካሂዷል።

በመድረኩ ላይ ንግግር ያደረጉት የሴቶችና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ በሀገራችን አብዛኛው ቁጥር ያላቸው ወጣቶች ላይ የአልኮል መጠጥ፣ የሲጋራ፣ የሺሻ፣ የአደንዛዥ እፆች ሱስ ተጠቂነት በከፍተኛ ፍጥነት እየተስፋፋ የመጣ አሳሳቢ ችግር ነው ብለዋል። በዚህም ታዳጊዎችና ወጣቶች ለትምህርታቸውና ለሥራቸው ትኩረት እንዳይሰጡ በማድረግ ከፍተኛ አዕምሮአዊና ስነልቦናዊ ጫና እንዲፈጠርባቸው እያደረገ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

እንደ ሚኒስትሯ ገለጻ ሱስ ስንፍና፣ ጭንቀት፣ ብስጩነት፣ እንቅልፍ ማጣት፣ እራስን ማጥፋትና ሌሎችም ውስብስብ ስነ-ልቦናዊ ችግሮችን የሚያስከትል ከመሆኑም ባሻገር በቤተሰብና በማህበረሰብ መካከል ግጭትና ስጋት እንዲፈጠር፣ ሰላምና መረጋጋት እንዳይኖር፣ የወንጀል ድርጊቶች እንዲበራከቱ ዋነኛ ምክንያት እየሆነ ይገኛል።

ሚኒስቴሩ አሉታዊ መጤ ልማዶችንና የሱስ ተጠቂነትን ለመከላከል ትኩረት በመስጠት የሚሠራ መሆኑን የገለጹት ዶክተር ኤርጎጌ፤ የወጣቶች ስብዕና ልማት ማዕከላትንና የሱስ ህክምና አገልግሎት መስጪያና የማገገሚያ ማዕከላትን በማቋቋምና በማጠናከር ወጣቶች ወደ ሱስ እንዳይገቡና በሱስ የተያዙትም እንዲያገግሙ በቅንጅት የሚሠራ መሆኑን ጠቁመዋል።

ዶክተር ኤርጎጌ ትውልድ የሚያጨነግፍ አደገኛ ድርጊት ያሉትን ሱስ ለመቀነስና ለመከላከል የሚደረገውን ሁለንተናዊ ጥረት ሁሉም የህብረተሰብ ክፍሎች በመደገፍና በመተባበር ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ጥሪ አቅርበዋል። ወጣቶች ሱሰኝነት በእኔ አይሰለጥንብኝም ብለው በሰለጠነ ንጹህ ማንነት ለእራሳቸውና ለቤተሰቦቻቸው የሚተርፍ ማንነት እንዲገነቡ አደራ ብለዋል።

በመድረኩ ንግግር ያደረጉት የኢትዮ ኢንጅነሪንግ ሥራ አስፈጻሚ አምባሳደር ምስጋኑ አርጋ፤ ወጣቶች ጊዜን ለማሳለፍ ብለው የሚጀምሩት ሱስ እድሜን በአጭር እያሳጠረና ወንጀል እያሰራ እድሜያቸውን በእስር ቤት እንዲያሳልፉ እያደረገ ይገኛል ብለዋል።

ቴክኖሎጂ በአግባቡ ካልተያዘ የሚኖረው ተጽእኖ ከፍተኛ ነው ያሉት ሥራ አስፈጻሚው፤ ማህበራዊ ሚድያ ለምርታማነትና መልእክት ለማስተላለፍ ጠቃሚ ቢሆንም አጠቃቀሙ በልክ ሊሆን እንደሚገባ ጠቁመዋል። ይህ ሳይሆን ሲቀርና ሰዎች በማህበራዊ ሚድያ ሱስ ሲጠመዱ ከሰው ጋር የሚኖረውን ተግባቦት ይቀንሳል፤ ቁጡ ያደርጋል፤ ለድብርት ይዳርጋል፤ ጥገኝነት ያመጣል፤ የእንቅልፍ ሰዓትን በመሻማት የሥራ ምርታማነትን ይቀንሳል ብለዋል።

አምባሳደር ምስጋኑ ወጣቶች ያሰቡበት ስኬት ላይ ለመድረስ መንግስት ቤተሰቤ ይሄን ስላላደረገልኝ ነው የሚል ሰበብ ከመደርደር በመራቅ ለራስ ሕይወት ወጣቱ ኃላፊነት መውሰድ እንዳለበት ጠቁመዋል።

16ኛው የአፍሪካ ወጣቶች ወር በሀገራችን ከጥቅምት 22 ጀምሮ "የወጣቶች ንቁ ተሳትፎና ተካታችነት ለስብእና ልማት" በሚል መሪ ቃል በየሳምንቱ በአራት የተለያዩ ከተሞች በተዘጋጁ የማነቃቂያ መድረኮች ተከብሯል። የማጠቃለያ መድረኩም የአደንዛዥ እጽ በወጣቶች ስብእና የሚያስከትለውን ተጽእኖ መከላከል በሚል መሪ ቃል የተካሄደ ነው።



ከስምምነቱ ወዲህ ከ70 ሺህ ሜትሪክ ቶን በላይ ድጋፍ ቀርቧል

# የመንግስት ያልተቋረጠ የሰብአዊ ድጋፍ ከችግር ታድጎናል

*- የሽሬ ከተማ ነዋሪዎች*

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የመንግስት ያልተቋረጠ የሰብአዊ ድጋፍ ከችግር ታድጎናል ሲሉ ለኢዜአ አስተያየታቸውን የሰጡ የሽሬ ከተማ ነዋሪዎች ተናገሩ።

መንግስት ሰላምን ለማረጋገጥ የሚያደርጋቸውን መልካም ጥረቶች በማድነቅ ከሰብአዊ ድጋፍ ባሻገር መሰረታዊ አገልግሎቶችን መልሶ በመገንባት ወደ ስራ ለማስገባት የሚያከናውነው ተግባር ተጠናክሮ እንዲቀጥልም ጠይቀዋል።

የፕሪቶሪያውን የሰላም ስምምነት ተከትሎ በትግራይ ክልል ሁሉም አካባቢዎች መንግስት ያልተቋረጠ የሰብአዊ ድጋፍና የመልሶ ማቋቋም ስራ እያከናወነ ሲሆን መሰረታዊ አገልግሎቶችን ለማስጀመርም በከፍተኛ ጥረት ላይ ይገኛል። የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን በሰጠው መረጃ ከሰላም ስምምነቱ በኋላ 70 ሺህ ሜትሪክ ቶን ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችን ለክልሉ ተደራሽ አድርጓል።

ከሽራሮ እስከ አድዋ ባለው አካባቢ ብቻ ከ535 ሺህ በላይ ዜጎች ሰብዓዊ ድጋፍ እንዲያገኙም ተደርጓል። በአጠቃላይ ከሰላም ስምምነቱ በኋላ በመንግስት እየተደረገ ያለውን የሰብአዊ ድጋፍ ተደራሽነትና ሌሎች ስራዎችን በተመለከተ ኢዜአ ያነጋገራቸው የሽሬ ከተማ ነዋሪዎች አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

አስተያየት የሰጡት የአካባቢው ነዋሪዎች በትግራይ ክልል የመንግስት ያልተቋረጠ የሰብአዊ ድጋፍ ከችግር ታድጎናል ብለዋል። የሰላም ስምምነቱን ተከትሎ በመንግስት በኩል የምግብ፣ የመድሃኒትና የህክምና ቁሳቁሶች በስፋት ባይገቡ ኖሮ የበርካቶች ህይወት ከፍተኛ ችግር ላይ ይወድቅ እንደነበርም ተናግረዋል።





በመሆኑም የመንግስት ቁርጠኝነትና እያደረገ ያለው ያልተቋረጠ ድጋፍ የሚመሰገንና የሚደነቅ ተግባር መሆኑን አስተያየት ሰጭዎቹ ገልጸዋል።

መንግስት ለዜጎቹ እያደረገ ያለው ያልተቋረጠ ሰብዓዊ ድጋፍ እንዳለ ሆኖ መሰረታዊ አገልግሎቶችን ስራ ለማስጀመር የሚደረገው ጥረት ተጠናክሮ እንዲቀጥል ጠይቀዋል። በኢትዮጵያ አደጋ ስጋት አመራር ኮሚሽን የኮሚሽነሩ ጽህፈት ቤት ኃላፊና የድጋፉ ጊዜያዊ አስተባባሪ ዘሪሁን ዘውዴ፤ ከሽራሮ እስከ አድዋ ባለው አካባቢ ብቻ ለ535 ሺህ ዜጎች የሰብዓዊ ድጋፍ ተደራሽ መደረጉን አረጋግጠዋል።

በትግራይ ክልል የሰብዓዊ ድጋፍን ተደራሽ ለማድረግ የመንግስት ጥረት ተጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑንም ተናግረዋል።

ዜና

# ጉባኤው አፍሪካ የበይነ መረብ ተደራሽነትን በማስፋት የኢኮኖሚ እድገትን ለማስመዝገብ ትልቅ ግብዓት ያገኘችበት ነው

## - ተሳታፊዎች

**ሞገስ ተስፋ**


አርሰኔ ቶጋኔ


ኢሊና ችጎስታኔ


ሞሰስ ማዮር

ፎቶ - በጸሐይ ንጉሴ

አዲስ አበባ፡- በ17ኛው የዓለም የበይነ መረብ አስተዳደር ጉባኤ አፍሪካ የዘርፉን ተደራሽነት በማስፋት የኢኮኖሚ እድገት ለማስመዝገብ ለምታደርገው ጥረት ትልቅ ግብዓት ያገኘችበት መሆኑን አስተያየታቸው ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የሰጡ የተለያዩ የአፍሪካ አገራት ተሳታፊዎች ገለጹ። ጉባኤው አፍሪካ ሌሎች አለም አቀፍ ሁነቶችን ማስተናገድ እንደምትችል ያሳየ ነው ብለዋል።

የሞዛምቢክ የኢንፎርሜሽን አስተዳደር ዳይሬክተር ኢሊና ችጎስታኔ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ባዘጋጀችው 17ኛው የበይነመረብ አስተዳደር ጉባኤ ላይ በኢንተርኔት አጠቃቀምና ተደራሽነት ዙሪያ በመወያየት ቀጣይ የመፍትሔ ሀሳብ ለማፍለቅ ትልቅ እድል የሰጠ ነው። በዘርፉ ያሉ ችግሮችን ለመቅረፍ መፍትሔ ማበጀት እንደሚገባም ፍንጭ የተገኘበት ነው።

በጉባኤው የተመላከቱ የመፍትሔ ሀሳቦችን በመያዝ ወደየአገራችን በመውሰድ ተግባር ላይ ለማዋል ቁልፍ ሀሳቦች ተነስተዋል ያሉት ዳይሬክተሯ፤ ሁነቱ የበይነመረብ ተደራሽነት ችግርን ለመቅረፍ በሚደረገው ጥረት መደላድል የሚፈጥር መሆኑንም ገልጸዋል።

እንደ ኢሊና ችጎስታኔ ገለጻ፤ አፍሪካ በኢንተርኔት አጠቃቀምና በሳይበር ደህንነት ዙሪያ እየተቸገረች ነው። አፍሪካውያን መፍትሔዎች ላይ አተኩረው መስራት አለባቸው። የኢንተርኔት ተደራሽነትን ማሳደግና በተለይም በገጠር ውስጥ የሚኖሩ ህዝቦችን ተደራሽ ማድረግ ለሚፈለገው እድገት እውን መሆን አጋዥ ነው።

አፍሪካ "የሶላር ኢነርጂን በመጠቀም የኢንተርኔት ተደራሽነትን በገጠራማው ክፍሏ ተደራሽ ለማድረግ ያላትን ዕምቅ ሀብት መጠቀም አለባት። መሰረተ ልማትን ማሳደግ በይነመረብን ተደራሽ በማድረግ አፍሪካን በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና በሌሎች ዘርፎች መለወጥ አስፈላጊ ነው" ብለዋል።

የዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ኮንጎ ሩዲ አለም አቀፍ ዋና ዳይሬክተር አርሰኔ ቶንጋሊ፤ ጉባኤው ጠቃሚ የሆኑ ልዩ ልዩ ይዘት ያላቸው አጀንዳዎች የተነሱበት ነው ብለዋል። የበይነመረብ ተደራሽነት፣ ትስስር መፍጠር፣ የሰብአዊ መብት፣ የኢንተርኔት አገልግሎት መቋረጥንና ሌሎች አህጉራዊና አለም አቀፍአዊ ጉዳዮን የተመለከቱ ውይይቶች ተካሂደዋል። እንደ አህጉር ለማደግ የበይነመረብ ተደራሽነትን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው ብለዋል።

የሳይበር ወንጀልን ለመከላከል የአቅም ግንባታ ስራ መስራት ይገባል ያሉት አርሰኔ፤ ማህበረሰቡን ከይሳበር ጥቃት ራሱን መከላከል የሚችል እንዲሆን ከትምህርት ቤት ጀምሮ መስራት ወሳኝ ነው ብለዋል።

የደቡብ ሱዳን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አማካሪና ዳኛ ሞሰስ ማዮር በበኩላቸው እንደገለጹት፤ 17ኛው የበይነመረብ አስተዳደር ጉባኤ በጣም ወሳኝና አስፈላጊ ጉባኤ ነው። አፍሪካ ባላት አቅም ልክ ለማደግ ብዙ መስራት ይጠይቃታል። እየፈተናት ያለውን ድህነት ለማስወገድ በይነመረብን ለበጎ አላማ ማዋል ይገባታል።

በይነመረብ ለኢኮኖሚ ዕድገት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። በበይነመረብ ህዝቦችን ለማስተሳሰር ፖሊሲ እስከ ማሻሻል የሚደረስ ስራ መስራት አስፈላጊ ነው። የኤሌክትሪክ አገልግሎትን በማስፋት የኢንተርኔት አገልግሎትን ማዳረስ አስፈላጊ ነው። ይህ ሲሆን አፍሪካ በኢኮኖሚ ትለወጣለች ሲሉም ገልጸዋል።

ተሳታፊዎቹ ኢትዮጵያ ጉባኤውን በተሳካ ሁኔታ ማስተናገዷ አፍሪካ ሌሎች አለም አቀፍ ሁነቶችን ማስተናገድ እንደምትችል ያስመሰከረ መሆኑንም ጠቁመዋል።

# ኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ፓርኮቿን ከወደብ አማራጮች ጋር ለማገናኘት ማቀዷ አዋጭ አካሄድ ነው

**ጌትነት ተስፋማርያም**


ረዳት ፕሮፌሰር ማቲዎስ እንሰርሙ


ፎቶ ሃዱሽ አብርሃ

ዶክተር ቤንጃሚን

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ፓርኮቿን ከወደብ አማራጮች ጋር በመሰረተ ልማት ለማገናኘት ማቀዷ የሚመከርና አዋጭ አካሄድ መሆኑን የሎጂስቲክስ ምሁራን ገለጹ።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቴክኒካል ዩኒቨርሲቲ ከሆነው የጀርመኑ በርሊን ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ያዘጋጀው በሎጂስቲክስ ዘርፍ የምስራቅ አፍሪካ ፈተናዎችና የመፍትሄ ሃሳቦች ላይ ያተኮረ መድረክ ትናንትና በአዲስ አበባ ተካሂዷል።

የቴክኒካል ዩኒቨርሲቲ ኦፍ በርሊን የዓለም አቀፍ የሎጂስቲክስ ኔትወርክ ውድድር ማዕከል ኃላፊ ዶክተር ቤንጃሚን ኒቼ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የኢትዮጵያ ቀጣይ የባቡርና ሌሎች መሰረተ ልማቶች ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ጋር የተገናኙ ናቸው።

በተለያዩ አካባቢዎች ላይ የተገነቡትን የኢንዱስትሪ ፓርኮች በባቡር መሰረተ ልማት ከወደብ አማራጮች ጋር ለማገናኘት መታቀዱ ገቢና ወጪ ምርቶችን በፍጥነት ወደወደብ ለማድረስ የሚረዳ ተመራጭ አካሄድ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ዶክተር ቤንጃሚን እንዳስታወቁት፤ የኢትዮጵያ ወጪና ገቢ ምርቶች በዋነኛነት 90 በመቶው የሚሆኑት ምርቶች የሚገቡት በጅቡቲ ወደብ በኩል ነው።

በመሆኑም የገቢና ወጪ ምርቶችን በፍጥነት ለመጠቀምና ለገበያ ለማቅረብ ቀልጣፋ የወደብ አገልግሎት፣ ፈጣን የገቢዎችና ጉምሩክ አሰራር እንዲሁም ጊዜ ቆጣቢ የትራንስፖርትና ተያያዥ አሰራሮች መስፋፋት አለባቸው ሲሉ ገልጸዋል።

ቀልጣፋ የወጪ ገቢ ንግድና ሎጂስቲክስ አሰራርን ለመተግበር ደግሞ ምርት የሚመረትባቸው ፓርኮችን ከደረቅ ወደብና ከባህር ወደብ ጋር በፍጥነት የሚገናኙባቸውን መሰረተ ልማቶች ማስፋፋት ያስፈልጋል። በዚህ ረገድ ቀጣዩ የኢትዮጵያ የባቡር መስመር ፍኖተ ካርታ ወደተግባር ሲገባ በጎ ውጤት ይዞ እንደሚመጣ ይገመታል ብለዋል።

በተለይ በዘርፉ ሰፊ ልምድ ካላት ጀርመን ብዙ መማር ይገባል ያሉት ዶክተር ቤንጃሚን፤ የኢኮኖሚ ዕድገትን ለማፋጠን በተለይም ቢዝነስ ለማሳደግ እና የሎጂስቲክስ ወጪዎችን ለመቀነስ የሚጠቅም ቴክኖሎጂ አገዝ ዲጂታላይዝ አሰራሮችን ጎን ለጎን መተግበር እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል።

የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምክትል ፕሬዚዳንትና የሎጂስቲክስ ተባባሪ ፕሮፌሰር ማቲዎስ ኢንሰርሙ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ምርታማነት ከባህርና ሎጂስቲክስ ድርጅቶች፣ ከጉምሩክና ታክስ አገልግሎት፣ ከትራንስፖርትና ከተለያዩ ሴክተሮች ጋር የተያያዘ ነው።

በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ፓርኮችን ከመገንባት ባለፈ የተለያዩ አስፈላጊ መሰረተ ልማቶችን በማቅረብ ረገድ ያሳየችው ጅማሮ መልካም ነው ሲሉ አስረድተዋል።

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ምርት ወደወደብ ሲላክ ብቃትና ፍጥነት ባለው መልኩ እንዲጓጓዝ ማድረግ የምርታማነትን አቅም ይጨምራል ሲሉ አስረድተዋል።

ኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ምርቶች ወደወደብ ለማመላለስ የሚረዱ መሰረተ ልማቶችን ከማሳደግ ባለፈ የድሬዳዋ ነፃ ቀጣናን በማቋቋም የጉምሩክ አሰራሮችን ዲጂታላይዝ በማድረግ ሎጂስቲክሱን ለማቀላጠፍ የምታከናውነው ስራ አበረታች መሆኑን ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ መንግስት ኢንዱስትሪዎችና ሎጂስቲክ ዘርፎችን በተጓዳኝነት ለማሳደግ እያከናወነ ያለው ጥረት ለመደገፍ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የበኩሉን ጥረት እያደረገ መሆኑንም ረዳት ፕሮፌሰር ማቲዎስ ገልጸዋል።

# የአካል ጉዳተኞችን ተጠቃሚነትና ተሳታፊነት ለማረጋገጥ ባለድርሻ አካላት ርብርብ እንዲያደርጉ ጥሪ ቀረበ

**ፋንታነሽ ክንዴ**


ፎቶ፡ በእዮብ ተፈራ

ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ

አዲስ አበባ፡- የአካል ጉዳተኞችን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነትና ተሳታፊነት ለማረጋገጥ ሁሉም ባለድርሻ አካላት ርብርብ እንዲያደርጉ የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ ጥሪ አቀረቡ፡፡

ዶክተር ኤርጎጌ ተስፋዬ ዓለም አቀፍ የአካል ጉዳተኞች ቀን አከባበርን በተመለከተ መግለጫ በሰጡበት ወቅት እንደገለጹት፤ መንግሥት የአካል ጉዳተኞችን ተጠቃሚነትና ተሳታፊነት ለማረጋገጥ የሕግ ማዕቀፎችን ከማሻሻል ጀምሮ በርካታ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል፡፡

የአካል ጉዳተኞች ሁለንተናዊ ችግሮች በመንግሥት ሥራ ብቻ መፍትሔ ስለማያገኙ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የአካል ጉዳተኞችን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነትና ተሳታፊነት ለማረጋገጥ የየበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ ጠይቀዋል፡፡

የአካል ጉዳተኞች ቀን መከበር ዋና ዓላማ የአካል ጉዳተኞች ላይ ያለውን ግንዛቤ ከፍ ከማድረግ ባሻገር አካል ጉዳተኞች ክብራቸው፣ መብታቸውና ጥቅማቸው ተጠብቆላቸው በፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዘርፎች እኩል ተሳታፊና ተጠቃሚነታቸውን ማረጋገጥ የሚያስችል ግንዛቤ ለመፍጠር የሚያስችል መሆኑን ጠቅሰው፤ በተጨማሪም በህብረተሰቡ ዘንድ የሚስተዋሉ የተዛቡ አመለካከቶችን ለመቀየር የሚያግዝ መድረክ መሆኑንም ጠቁመዋል፡፡

መንግሥት የአካል ጉዳተኞችን ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚነትና ፖለቲካዊ ተሳትፏቸውን ለማረጋገጥ እየሠራ መሆኑን አስታውሰው፤ በትምህርት፣ በጤና፣ በሥራ እድል ፈጠራና በሌሎችም መስኮች አቅማቸው ተገንብቶ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ በሚደረገው ሂደት የበኩላቸውን ድርሻ እንዲያበረክቱ እየተሠራ መሆኑንም አመልክተዋል፡፡

አካል ጉዳተኞች እንደ ማንኛውም ዜጋ የመከበርና የመጠቀም መብት እንዳላቸው ገልጸው፤ በተለይ የሕዝብ አገልግሎቶችን ለአካል ጉዳተኞች ተደራሽ ማድረግ በችሮታ የሚደረግ ሳይሆን ግዴታ መሆኑን በመገንዘብ ምቹ ሁኔታዎችን መፍጠር እንደሚገባ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል ብለዋል፡፡

የአካል ጉዳተኞችን ተሳታፊነትና ተጠቃሚነት ማረጋገጥ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ብቻ የሚሠራ እንዳልሆነ ጠቁመው፤ ሁሉም ሴክተሮች በሁሉም ዘርፍ የአካል ጉዳተኞችን አካታችነትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ተቋማዊ በሆነ መንገድ መሥራት እንዳለባቸው አስገንዝበዋል፡፡

የኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ማኅበራት ፌዴሬሽን ዋና ዳይሬክተር አቶ አባይነህ ጉጆ በበኩላቸው፤ የአካል ጉዳተኞች ቀን የሚከበርበት ዓላማ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የተደነገጉ የአካል ጉዳተኞች ሁሉን አቀፍ መብቶች እንዲከበሩ ለማስቻል መሆኑን ገልጸዋል፡፡

አካል ጉዳተኞች በሁሉም የልማት መስኮች እኩል እድል አግኝተው በሚገባ ተሳታፊና ተጠቃሚ እንዲሆኑ የኅብረተሰቡንና የሚመለከታቸው አካላትን ግንዛቤና ተሳትፎ ማሳደግ አስፈላጊ መሆኑን አውስተው፤ የበዓሉ መከበር አጠቃላይ የማህበረሰቡን ግንዛቤ በማሳደግ የአካል ጉዳተኞችን ጉዳይ ጉዳዩ እንዲያደርገው ትልቅ ሚና እንዳለው አስታውቀዋል፡፡

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የማኅበራትንና የፌዴሬሽኑን አቅም ለማጎልበትና ለማጠናከር የሚያስችሉ ስልጠናዎችን በማመቻቸት፣ ሰው ሰራሽ የአካል ድጋፎችን፣ የፋይናንስና የማቴሪያል እገዛዎችን እያደረገ መሆኑን በመጠቆም ምስጋና አቅርበዋል፡፡

ዓለም አቀፍ የአካል ጉዳተኞች ቀን በዓለም ለ31ኛ በኢትዮጵያ ደግሞ ለ30ኛ ጊዜ "አካታች የፈጠራ ሥራና ሽግግራዊ መፍትሔ ለኢትዮጵያ አካል ጉዳተኞች ሁለንተናዊ ተደራሽነት" በሚል መሪ ቃል ከህዳር 23 እስከ ህዳር 24 ቀን 2015 ዓ.ም በድሬዳዋ ከተማ እንደሚከበር ተገልጿል፡፡

## ማስታወቂያ ቁጥር: OCC/SL-01/2022)

# የአቅራቢዎች ዝርዝር ምዝገባ ማስታወቂያ

የኦሮሚያ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን ቀጥሎ ባለው ዝርዝር ውስጥ የተጠቀሱትን የዕቃዎችና አገልግሎት አቅርቦት ዘርፎች መስፈርቱን ማሟላት የሚችሉና ህጋዊ የንግድ ፍቃድ ያላቸውን አቅራቢ ድርጅቶችን ቀጥሎ ከ1-8 ተራ ቁጥር በተዘረዘሩ ነጥቦች ላይ በመመሥረት ብቁ አቅራቢዎችን (Potential Suppliers) በመምረጥ በሚመለከታቸው መደብ በአቅራቢነት ዝርዝር (Supplier List) ለአንድ ዓመት መዝግቦ በመያዝ በውስን ጨረታ ለሚፈጸሙ ጥቅል ግዥዎች፤ በፕሮፎርማ ግዥና በቀጥታ ግዥ ሂደቶች በማሳተፍ ግዥና አቅርቦትን ግልጽነት ባለው መንገድ ማከናወን ይፈልጋል፡ በመሆኑም ቀጥሎ በተጠቀሱት ዕቃዎችና አገልግሎቶችን ማቅረብ የምትፈልጉ ድርጅቶች ከዚህ በታች የተገለጹትን መስፈርቶች በማሟላት ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ዕለት ጀምሮ በ15 ተከታታይ ቀናት ውስጥ መመዝገብ የምትችሉ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

1. ከሚመዘገቡበት ዘርፍ ጋር ተዛማጅ የሆነ የታደሰ የንግድ ስራ ፈቃድ፣የመንግሥትን የግብር ግዴታ መወጣትን የሚያመለክት ማስረጃ (ታክስ ክሊራንስ)፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ሰርቲፊኬት እና የታክስ ከፋይ መለያ ቁጥር በማቅረብ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን አንስቶ ዘወትር በስራ ሰዓት መመዝገብ ይችላሉ፡፡
2. ድርጅታችሁ ከተመሰረተ ከአንድ አመት በላይ ያስቆጠረ ከሆነ በውጭ ኦዲተር የተሰራ የቅርብ ሁለት አመታት የፋይናንሻል አቅም ኦዲት (Financial capability Audit ) ሪፖርት ማቅረብና የድርጅታችሁን ገቢ ወጪ እንቅስቃሴ የሚያሳይ የቅርብ ሁለት ዓመት የተጣራ ካሽ ፍሎ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፤
3. ከተመሠረቱ የአንድ ዓመትና ከዚያ በታች ቆይታ ያላቸው ድርጅቶች የራሳቸውን ፋይናንሻል ስቴትመንት (Financial Statement) ማቅረብ አለባቸው፤
4. ተመዝጋቢ ድርጅት ቀደም ባሉት ጊዜያት በገባው ውል መሠረት ግዴታውን (በመጠን፤በጊዜና በጥራት) መወጣቱን የሚገልጽ የመልካም ውልና ሥራ አፈጻጸም ማስረጃ በተለይም ከኮንስትራክሽን ኩባንያዎች (ቢያንስ 3 ታዋቂ ኩባንያዎች) የሚያቀርብ የተሻለ ነጥብ ያስገኝለታል፤
5. አምራች ድርጅቶች የጥራት አመራር ሥርዓት (QMS of ISO 9001:2015 ) የተገበሩና ሠርተፊኬቱን ማቅረብ የሚችሉ ተጨማሪ ነጥብ በማግኘት ቅድሚያ ተመራጭ የመሆን ዕድል ያስገኛል፤
6. አምራች ድርጅቶች እና ከአምራቹ ህጋዊ ውክልና የተሰጣቸው አስመጪዎች እና ጅምላ አከፋፋዮች መሆናቸውን የሚገልጽ ማስረጃ (Manufacturer's Authorization Letter) ማቅረብ የሚችሉ ከሆነ ተጨማሪ የመመረጥ ነጥብ ያሰጣቸዋል፤
7. ተመዝጋቢ ድርጅቶች ኮርፖሬሽናችን የሚፈልጋቸውን ዕቃዎችና አገልግሎቶች በተፈለገው መጠን፤ጥራት፤ግዜ፤ቦታና ሁኔታ ለማቅረብ ፍቃደኛ እና ኃላፊነት የሚወስዱ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ደብዳቤ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፤ ይህም ተጨማሪ ነጥብ ለማስገኘት ያስችላል፤
8. ተመዝጋቢ ድርጅቶች ተወዳድረው ላሸነፉበት ዕቃዎች ከድርጅታችን ጋር የአመት (Framework contract Agreement) በመግባት የቅድሚያ ክፍያ ሳይከፈላቸው የአቅርቦት ሥራ በማከናውን ክፍያ ከአቅርቦት በኃላ ለመቀበል ፍቃደኛ መሆናቸውን ማስረጃ የሚያቀርቡ ተጨማሪ ነጥብ ይሰጣቸዋል፤
9. ተመዝጋቢ ድርጅቶች ተወዳድረው ላሸነፉት ዕቃዎች በተጠየቀው ቦታ ድረስ ለማቅረብ የትራንስፖርት አገልግሎት ለማቅረብ ፍቃደኛ ስለመሆናቸው ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ ከሆነ ተጨማሪ ነጥብ ያገኛሉ፤

በመሆኑም ተመዝጋቢዎች ምንም አይነት ክፍያ መክፈል ሣይጠበቅባቸው ከላይ የተዘረዘሩ መረጃዎችን አሟልተው በሰም በታሸገ ኢንቨሎፕ በማሸግ የኮርፖሬት ግዥ ቡድን በመገኘት ቅዳሜ እስከ ስድስት ሰዓት ጨምሮ ይህ ማስታወቂያ አየር ላይ ከዋለበት ቀን አንስቶ ባሉት 15 ተከታታይ ቀናት ድርጅቱ በሚገኝበት ቃሊቲ የመካኒኮችና ሾፌሮች ማሰልጠኛ ፊትለፊት ህንጻ 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 3 መመዝገብ የምትችሉ መሆኑን እየገለጽን ከተጠቀሰው ቀን ውጪ የሚመጡ ማንኛውም አቅራቢዎች ማስረጃ ተቀባይነት የሌለው መሆኑን እናሳውቃለን፡፡

| A. | Construction Materials & Light Equipment | | |
|---|---|---|---|
| 1 | Re-enforcement Bar, Black & Barbed Wire, Mesh Wire | 10 | Bitumen, Explosive Materials |
| 2 | RHS, CHS, LTZ, SHS, Angle Iron | 11 | HDPE Pipe & Fittings, DCI Pipe & fittings |
| 3 | Electrical Materials (Electrical Transformer, Distribution Boards, Wires, Power Cables, Electrical Poles, Fire Hose, Fire Resistance, Fittings & Lightings) | 12 | UPVC Pipe & Fittings, Steel Pipe & Fittings, GS Pipe & Fittings, GRP Pipes & fittings, PPR Pipe & fittings, Riser Pipe |
| 4 | Ceramics, Marbles, Skirting, Terrazzo, & Plastic Tiles, | 13 | Paints of different Types, Antirust, Gypsum & Stucco |
| 5 | Plastic & Steel Pipes, Geo-membrane & Water Stopper | 14 | Sanitary Materials & Fixtures (for Building Construction) |
| 6 | Plastic Pipes & Steel Pipes Fittings | 15 | Lumber, Purlin, Chip-wood, Traffic Sign Form Works, Cutting, Grinding Disc & Electrode. |
| 7 | CIS, EGA & Sheet Metals, Normal Nails & Roofing Nails, Ceiling Materials) | 16 | Construction Sand, Crushed Aggregate, Stone & Selected Materials |
| 8 | Cement Concrete, HCB & Bricks | 17 | Add Mixtures |
| 9 | Hand Tools | 18 | Light Equipment (Mixer, Generators, Water Pumps, Compressor, Total Station, GPS, e.t.c) |
| | | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| B. | Spare Parts, Tyres, Battery & Lubricants | F | Maintenance Service |
| 1 | Spare Parts for Earthmoving Machinery | 1 | Machinery & vehicles |
| 2 | Spare Parts for Vehicles of Different Types | 2 | Shopping Machine (Torno) |
| 3 | Spare Parts for Crushers Equipment | 3 | Radiator, fuel pump & upholstery (Tapestry) |
| 4 | Spare Parts for Light Plants | G | Services Providers |
| 5 | Tyres of Different Types (for Machinery & Vehicles) | 1 | Training & Examining Mechanics Technical Ability |
| 6 | Lubricants for Machinery, Vehicles & Light Plants | 2 | Aluminum Supply & Fixing Service, Glazing (Doors & Window Glass Supply & Fixing Services) |
| 7 | Battery of Different Types | 3 | Steel Gates & Wooden Products (Doors & Windows Supply With Fixing Service) |
| 8 | Car Decors & Floor Mats | 4 | Fixed Asset Evaluation & Revaluation Service |
| C. | Rental & Accommodation Provision Service | 5 | Car Trucking by GPS Service |
| 1 | Construction Machinery Rental Service | 6 | Fuel Consumption & Rate Normalization |
| 2 | Heavy & Light Vehicles Rental Service | 7 | Plant Erection, Testing & Commissioning |
| 3 | Currier Trucks Rental Service | 8 | Fuel Station Installation, Testing & Commissioning |
| 4 | Fuel Trucks Rental Service | 9 | Fuel Tank Volume Calibration |
| 5 | Crane & Lifting Service | 10 | Manpower Capacity Building Training Service |
| 6 | Hotel Hall & Entertainment Provision Service | 11 | Laboratory & Geo-technical investigation Service |
| D | Office Equipment & Furniture | 12 | Cars Technical inspection (Bolo) |
| 1 | Office Equipment (Computers, Printers, Scanners & Photocopy) | 13 | Electromechanical (Lift, mechanical Ventilation, e.t.c) supply & installation Service |
| 2 | Office Furniture | 14 | Printing Service, Film Production & Event Organizing Service |
| 3 | Office Electronics Equipment | H | Others if Any |
| E | Office & Employee's Supplies | 1 | |
| 1 | Stationery Materials | 2 | |
| 2 | Detergents of Different Types | 3 | |
| 3 | Uniforms (Cloths & Shoes) | 4 | |

**አድራሻ፡- ቃሊቲ የመካኒኮችና ሾፌሮች ማሰልጠኛ ፊትለፊት/ CCRDA ጎን**

+251-11-439-02-22 FAX. N0. 0114396476/0114390546/0114396594

# የኦሮሚያ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን

# ርዕሰ አንቀፅ

## የአገራዊ ምክክር መድረኩ ስኬት የሁሉንም ወገን ንቁ ተሳትፎ ይጠይቃል!

ኢትዮጵያውያን በመሬት፣ ራስን በራስ በማስተዳደር፣ በቋንቋ፣ በፖለቲካ ተሳትፎና በመሳሰሉት ጉዳዮች በየዘመናቱ ጥያቄዎችን ሲያነሱ ኖረዋል። ጥያቄዎቹ እየበረቱ ሄደውም አመጾችን፣ ግጭቶችንና የጦርነት ሁኔታዎች ሲፈጥሩ ቆይተዋል። በዚህ ብቻ ሳይገቱም የመንግስት ለውጦችን ፣ የህግ እና የአሰራር ማሻሻያዎችን ያስከተሉባቸው ሁኔታዎችም ነበሩ። በእነዚህም አንዳንዶቹን ጥያቄዎች መመለስ የተቻለበት ሁኔታ ነበር።

በንጉሱ ዘመን በተለይ በተማሪዎች ሲነሳ የነበረው የመሬት ላራሹ ጥያቄ በወታደራዊው መንግስት ርምጃ መፍትሄ ያገኘበትን ሁኔታ ለእዚህ በአብነት መጥቀስ ይቻላል፤ በአንጻሩ ዜጎች የፈለጋቸውን የፖለቲካ አመለካከት የመከተል መብት ሊኖራቸው ይገባል የሚሉ ወገኖች ያነሷቸው የነበሩ ጥያቄዎች በአግባቡ መፍትሄ ሳይገኙ ብዙ ዘመናትን ያሳለፉበት ሁኔታም እንዳለ ይታወቃል።

አንዳንዶቹ የዜጎች ጥያቄዎች ህገ መንግስታዊ መፍትሄ ቢያገኙም፣ መንግስታት ስልጣን ላይ ለመቆየት ሲሉ ሲፈጥሩ በነበረው የፖለቲካ ጫና ሳቢያ ያልተመለሱ ጥያቄዎች መሆናቸው ይታወሳል። ለዚህም የኢፌዴሪ ህገ መንግስት ዜጎችና ቡድኖች የፈለጋቸውን የፖለቲካ አመለካከት እንዲያራምዱ የደነገገበትን፣ መሬት ላይ የነበረው ሁኔታ ግን ይህን የሚጻረር ሆኖ የቆየበትን ሁኔታም መጥቀስ ይቻላል።

ለይስሙላ ካልሆነ በቀር አገራዊ ለውጡ እውን እስከሆነ ጊዜ ድረስ የመንግስት ስልጣን ከጨበጠው ፓርቲ ውጪ ያሉ ፓርቲዎች ከፍተኛ ጫና ሲደርስባቸው፣ መሪዎቻቸውና አባሎቻቸው ለግድያ፣ ለእስር፣ ለስደት ሲዳረጉ የነበረበት ሁኔታም ይህንኑ ያመለክታል።

ከአገራዊው ለውጥ አንስቶም በአገራዊ ጉዳዮች ላይ በጠረጴዛ ዙሪያ መወያየት እንደሚያስፈልግ ህዝቡ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ፣ አክቲቪስቶች፣ ወዘተ ሲጠይቁ ቆይተዋል። የመሬት፣ የህገ መንግስት፣ ራስን በራስ የማስተዳደር መብትና ሌሎች ጥያቄዎች ሲነሱ እንደቆዩ ሁሉ ዛሬም በተለያዩ መድረኮች ላይ ይነሳሉ።

በአገራችን ለተካሄዱ ግጭቶች፣ ጦርነቶችና አለመግባባቶች አንዱ ምክንያትም ዜጎችን በሚያወዛግቡ ጉዳዮች ላይ ራሳቸው ዜጎች መክረው መፍትሄ የሚያስቀምጡበት ሁኔታ አለመኖሩ ያሳሰበው መንግስት ይህን የሕዝብ የዘመናት ጥያቄ ለመመለስ እየሰራ ይገኛል።

የኢትዮጵያ መንግስት መፍትሔ ሳያገኙ ዘመናትን እየተሻገሩ እዚህ በደረሱት ሀገራዊ አጀንዳዎች ላይ ዜጎች መክረው መፍትሄ እንዲያስቀምጡ እንደሚሰራ ከሀገራዊ ለውጡ አንስቶ ነው በተደጋጋሚ ሲያረጋግጥ የኖረው፤ ይህንንም መሬት ላይ ለማውረድ አገራዊ የምክክር ኮሚሽን በማቋቋም ኮሚሽኑን የሚመሩ አካላትንም መሰየሙ ይታወሳል።

ኮሚሽኑ ከተቋቋመ ዘጠኝ ወራትን አስቆጥሯል፤ ሃላፊነቱን ለመወጣት እየሰራ እንደሚገኝ መረጃዎች ያመለክታሉ። ኮሚሽኑ የተለያዩ መድረኮችን ሲያካሂድ የቆየ ሲሆን፣ ሰሞኑን በሰጠው ጋዜጣዊ መግለጫም ተጨባጭ መረጃዎችን ለማግኘት ከትግራይ ክልል በስተቀር በክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች እየተዘዋወረ መስራቱን አስታውቋል።

የአገራዊ ምክክር መድረክ ውይይቱ በመጪው መጋቢት ወር እንደሚጀመርም ሰሞኑን አስታውቋል። ኮሚሽኑ እንዳለው፤ ለዚህም ዝግጅቶች እየተደረጉ ናቸው። በመጪው ከጥር እስከ የካቲት ወር ደግሞ አጀንዳዎች የመሰብሰብ ስራዎች ይከናወናሉ። ከየካቲት ወር እስከ መጋቢት ድረስ ደግሞ አጀንዳ የመቅረጽ ስራዎች እንደሚካሄዱ ከዚያም ወደ ውይይቱ ይገባል።

ሲጠበቅ የቆየው አገራዊ የምክክር መድረክ ሊጀመር የጥቂት ወራት እድሜ እንደቀሩት የኮሚሽኑ መረጃ ያመለክታል። የልሂቃንን ብቻ ሳይሆን የአጠቃላይ ህዝቡን ፍላጎት መሰረት ባደረገ መልኩ እንደሚካሄድ የሚጠበቀው ይህ የምክክር መድረክ እንዲሳካ መንግስት የበኩሉን ጥረት እያደረገ ይገኛል።

በምክክር መድረኩ በሚካሄዱ ውይይቶች የሚደረስባቸው ድምዳሜዎች አገሪቱ ለተያያዘችው ልማትን የማፋጠን፣ ዘላቂ ሰላምን የማረጋገጥ ተግባር ወሳኝ ናቸው። ውይይቶቹ ዜጎች ለዘመናት ሲጠብቋቸው የቆዩ እንደመሆናቸው የቆዩና ሲንከባለሉ የመጡ ስር የሰደዱ ችግሮችን የያዙ አጀንዳዎች የሚነሱባቸውና መፍትሄ የሚመላከቱባቸው መሆናቸው ይጠበቃል።

ይህን መድረክ መጠቀም የአገርን የዜጎችን የወደፊት እጣ ፈንታ መወሰን ይሆናል። ዜጎች መግባባት በሚችሉባቸው አጀንዳዎች ላይ እንዲግባቡ፣ ሊግባቡ በማይግባቡባቸው ላይ ደግሞ ልዩነቶቻቸውን ጠብቀው ተከባብረው ሊቀጥሉ የሚችሉበትን ሁኔታ የሚፈጥረው የአገራዊ ምክክር መድረክ ውይይቶች እንዲሳኩ ማድረግ ያስፈልጋል።

መንግስት እንደ መንግስት አገራዊ የምክክር መድረኩ እንደሚካሄድ ቃል በመግባት፣ ለዚህም ኮሚሽን በማቋቋም ወደስራ እንዲገባ በማድረግና አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ እያረጋገጠ ይገኛል። በቀጣይም ይህንኑና መሰል ድጋፎችን እንደሚያደርግ ይጠበቃል። በአገራዊ አጀንዳዎች ላይ ምክክር እንዲደረግ ሲጠይቁ የኖሩ ኃይሎች በሙሉ ያ ወቅት ደርሷልና ለውይይቱ ዝግጁ መሆን አለባቸው።

ዜጎች፣ የፖለቲካ ኃይሎች፣ ዲያስፖራዎች፣ በአጠቃላይ መላው ህዝብ ንቁ ተሳትፎ ለማድረግ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል። ኮሚሽኑ አጀንዳ ለመሰብሰብ ከሚንቀሳቀስበት ወቅት አንስቶ ውይይቱ በሚካሄድበት ወቅት ተሳትፏችሁ ወሳኝ መሆኑን በመገንዘብ ለስኬታማነቱ መረባረብ ይገባል።

ከአገራችን ታሪክ መረዳት እንደሚቻለው ለሀሳብ ልዩነቶች ሁሉ መፍትሄው አመጽ፣ ጦርነት ሆኖ ቆይቷል፤ ይህ ገጽታ መቀየር ይኖርበታል፤ ይህን ለመቀየር ደግሞ ይህ የምክክር መድረኩ ታላቅ ዕድል ነው። መድረኩ ከብዙ ጥያቄና ትግል በኋላ የተገኘ ታላቅ መድረክ ነው። ይህን መድረክ በመጠቀም አገር ችግሮቿን በውይይት የምትፈታበትን፣ ግጭትና ጦርነት አማራጭ የማይሆኑበትን መንገድ መቀየስ ከሁሉም ወገን ይጠበቃል።

መንግስት ለሰሜኑ ጦርነት ዘላቂ ሰላም ለማምጣት ከመጀመሪያው አንስቶ ሰላማዊ አማራጭን ይዞ ሲሰራ ቆይቷል። ይህ ቁርጠኝነቱ ፍሬያማ እየሆነ ይገኛል። በአገራዊ ምክክር መድረኩ በሚካሄዱ ውይይቶችም ይህን ዘላቂ ሰላም መትከል የሚያስችሉ አጀንዳዎችን በማንሳትና ገንቢ ውይይት ማድረግ ይገባል!

ኢፕድ

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70

**ነፃ ሃሳብ**

**ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው። በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም።**

## እንግዶቹ ባንኮችና ተጠባቂው ማህበራዊ አገልግሎታቸው

ግርማ መንግሥቴ

የዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት፣ በተለይም ባንኮች ኢትዮጵያ ውስጥ በሕጋዊ ማዕቀፍ ላይ በተመሰረተ መልኩ እንዲሳተፉ በኢትዮጵያ በኩል በሩ ተከፍቷል። አዋጁም ጸድቋል። በዚሁ መሰረት (እስካሁን ባለው መረጃ መሰረት) ስመ-ጥር ዓለም አቀፍ ባንኮች፣ በተለይም ምዕራብ ተኮር የሆኑቱ የአዋጭነት ጥናታቸውን በይፋ ከጀመሩ ሰንብተዋል።

በጉጉት ሲጠብቁት የነበረው የ"ይግቡ" በር በመከፈቱ ምክንያት ጉጉታቸውን ወደ ተግባር ለመለወጥ ያስችላቸው ዘንድ በአዲስ አበባ ጽሕፈት ቤታቸውን የከፈቱትና የአዋጭነት ጥናት እያደረጉ ካሉት መካከል በአየር ንብረት ለውጥ ላይ የሚከናወኑ ተግባራትን በመደገፍ ቁጥር አንድ የሆነውና ንብረትነቱ የህብረቱ አገራት የሆነው European Investment bank፤ በደቡብ አፍሪካ እውቅናን ያተረፈው ስመጥሩው Standard bank፤ የጀርመኑ ቱጃር Commerz bank፤ ኖይሮቢ ያለውና የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አይነቱ KCB bank ተጠቃሽ ናቸው።

ዋና መቀመጫውን ካዛብላንካ ያደረገውና በ18 የአፍሪካ አገራት ቅርንጫፎች ያሉት Bank of Africa (BOA)፤ በ1863 የተመሰረተው፣ 1ሺህ 773 ቅርንጫፎች ያሉትና ንብረትነቱ የቱርክ መንግስት የሆነው Ziraat Ban፤ አገራት በአክሲዮን ያቋቋሙትና መቀመጫውን ፍራንክፈርት ያደረገው Deutsche Bank፤ በ"Tier 1 capital" በ(capital + reserves + retained earnings + minority interests ላይ የተመሰረተ) መለኪያ ከምስራቅ አፍሪካ አንቱ የተባለውና የ$1.6 ቢሊዮን ካፒታል ባለቤት የሆነው Equity Bank Group ሌሎቹ ናቸው።

ለወጪ ንግድ በማበደር የሚታወቀውና የደቡብ ኮሪያ ንብረት የሆነው South Korean Exim Bank (Korea Eximbank በሚልም ይታወቃል)፤ የህንድን የወጪ ንግድ ይደግፍ ዘንድ በፓርላማው ፀድቆና በ1982 ተመስርቶ ወደ ስራ የገባው Export-import Bank of India እና የመሳሰሉትም ይጠቀሳሉ።

በምስራቅ አፍሪካ እየመሩ ያሉት ባንኮችም ከኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ጋር እስከ መምከር ድረስ መዝለቃቸው እየተሰማ ይገኛልና ተስፋችን ትልቅ ነው። የትልቅነቱ መለኪያ ድጋሚ ከዚህ በታች የምናወራው እውን ሲሆን ነው።

እንዳለመታደል ሆኖ እኛ አገር ሀብት ሲገኝ ያንን ሀብት ወደ ሌላ ሀብት የመቀየር፣ በተገኘው ሀብት ተጠቅሞ ለዜጎች የስራ እድል የመፍጠር ነገር አልተለመደም፤ ወይም አይታወቅም። የግል ባንኮች (Domestic banks) ሳይቀሩ ሰኔ ግም ባለ ቁጥር ትርፋቸውን ሸንሽነው ከመከፋፈል ውጭ የውጪ ባንኮች (Foreign banks) ገብተው እንዳያሽመደምዱን ብለው ሲሰጉና ትርፋቸውን ወደ ካፒታላቸው ማሳደጊያነት ሲያዞሩ እንኳን ብዙም አይታዩም።

የሁሉም አጠቃላይ (ካፒታል) አቅም የንግድ ባንክን ሩብ ያህል ለመድረስ እንኳን አልደረሰም። በግል ቢዝነስ የተሰማሩትም ቢሆኑ ትርፍ ሲያገኙ ወደ "ቪ8" እና ከፍ ሲልም "ሀመር" ላይ ሲያፈሱት እንጂ እስኪ ለአንድ ለ50 ሰው እንኳን የስራ እድል ልፍጠር ብለው የጎጆ ኢንዱስትሪን የምታክል "ጎጆ" ሲያቋቁሙ አይታዩም። ዝርዝሩ ብዙ ነውና ወደ ጉዳያችን እንመለስ። ተመልሰንም የባንኮችን ሚናና የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ እንመልከት።

ባንኮች (የMicrofinance ባንኮቹ እንዳለ ሆኖ) ከተቋቋሙበት ዋና ዋና አላማዎች ባሻገር ከፍተኛ የሆነ ማህበራዊ ሀላፊነትም ያለባቸው ሲሆን፤ አንዱም ከማበደር ባለፈ ለዜጎች የስራ እድል መፍጠር ነው።

ሰፋፊ የስራ እድሎችን የመፍጠር ግዴታ ያለባቸው ባንኮች፣ ይህ ሀላፊነት በራሳቸው ቋንቋ ሲገለፅ "Banks provides loans for skill development and contributes towards job opportunities." በሚል ሲሆን፤ እዚህ ሲመጡ እንዳይረሱት እንጂ ለዜጎች የስራ እድል የመፍጠር ግዴታ አለባቸው። ጉዳዩ በአገራቸው የተለመደ እንደ መሆኑ መጠንም እንደሚያደርጉት ጥርጥር የለም።

ማርች 2020 ይፋ በሆነ፣ በሰንጠረዥ የተደገፈና "Job creation scenario in the banking sector" በሚል ርእስ የቀረበ ጥናት እንደሚያሳየው ባንኮች በያሉበት የስራ እድል መፍጠር ተግባር ላይ የተሰማሩ ሲሆን በተለይም አስፈላጊ በሆኑ መስኮች በአውቶሜሽን፣ ምርትና ምርታማነትን በተመለከተ፣ በመቆጠብና ቁጠባን በማሳደግ፤ አመለካከትን በመቀየር፤ የመንግስት የስራ ፈጠራ ተግባራትን በማገዝ፤ ስልጠናዎችን በመስጠት፤ ክሂሎትን የማዳበር ስራዎችን በመስራት፤ የስራ ፈጠራ አቅምን በማጎልበት ወዘተርፈ ላይ ያሳዩት ተሳትፎና ያስገኙት ውጤት በስኬታማነታቸው ተመዝግቦላቸዋል።

በ2022ም 100 ሚሊዮን የስራ እድሎችን ይፈጥራሉ ተብሎ በእቅድ ተይዞ ያሳኩታል ተብለው እየተጠበቁ ሲሆን፤ አመቱ ተጠናቅቆ በ2023 የእቅድ አፈፃፀማቸው ይፋ ሲሆን የምንገነዘበው ይሆናል። ይህ ወደዚህ ከሚመጡትም ሆነ እየመጡ ካሉት ይጠበቃልና እኛም እድሉን ለመጠቀም፤ እነሱም እድሉን ለመፍጠር፤ ሁለታችንም መዘጋጀት አለብን ማለት ነው። (ይህ ባንኮች በተለያዩ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ... ጉዳዮች ላይ የሚያደርጉትን፣ (ለምሳሌ የትምህርት፣ የጤና ... ተቋማት ግንባታን፤ በባንኮቹ ውስጥ ቀጥረው የሚያሰሯቸውን ... የስፖንሰርሺፕ ድጋፍ የሚያደርጉትን እንደማያካትት ልብ ይሏል።)

በዚህ መስክ ተጠቃሽ ከሆኑት አገራትና የባንክ ኢንዱስትሪዎች መካከል (ያንን አድርጎ እንኳን "በቂ ነው" አልተባለለትም) አንዷ ባንግላዴሽ ስትሆን ባለፈው አመት ብቻ በግል ባንኮች ከ182ሺህ 610 በላይ የስራ እድል ለዜጎች የተፈጠረባት አገር ሆና ተመዝግባለች። ባንኩም "የስራ እድሎችን የፈጠረ ..." ተብሎ ተይዞለታል።

በአመቱ ውጤታማ ከተባሉት ባንኮች መካከል የህንዶቹ (State Bank of India, Bank of Baroda, Punjab National Bank, IDBI Bank ... እና የመሳሰሉት) የሚገኙበት ሲሆን ለዚህ ካበቋቸው ተግባራቶቻቸው መካከልም አንዱ ይኸው ለዜጎች የስራ እድል መፍጠራቸው መሆኑን መዘንጋት አይገባም፤ ከመጪዎቹ እንግዶቻችን ባንኮችም ይህንን መጠበቅ የዋህነት አይደለም፤ የማይገባንም መሻት ተደርጎ ሊወሰድ አይገባም።

በአንፃሩ፣ መጪዎቹ ባንኮች ይህንን ወሳኝ ተግባር በእቅዶቻቸው ይዘው፤ የሰው ኃይልና በጀት መድበው ሊሰሩበት ነው የሚገባው። መንግሥትም ሆነ ሌሎች የሚመለከታቸው አካላትም ባንኮቹን ሲመዝኑ መስፈርቶቻቸው እነዚህን ሊያካትቱ ይገባል።

እንደ ዓለም ባንክ መረጃ መሰረት ባንኮች አገራት ከድህነት እንዲወጡ የማድረግ፣ የማገዝ ... ከፍተኛ ሀላፊነት አለባቸው። በተለይም የዩኤንን ስትራተጂያዊ የልማት ግብ ተግባራዊ ከማድረግ አኳያ ባንኮች ቁልፍ ሚና መጫወት የሚጠበቅባቸው መሆኑን ተገልፆ ይገኛል።

ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው ባንኮች ከአትራፊነት ተልእኳቸው በዘለለ ማህበራዊ አገልግሎት መስጠትና በአገራት የልማት ተግባራት ላይ መሳተፍ አንዱ ተግባራቸው መሆኑን ሲሆን፤ ይህ ካልሆነ ዜማና ግጥሙን ውሀ በላው ማለት ነው ፤ ይህ እንደማይሆን ተስፋ እናደርጋለን።

ዜና


ዶክተር ሳሙኤል ክፍሌ

# የዩኒቨርሲቲ መውጫ ፈተና በኦንላይን ለመስጠት ዝግጅት እየተደረገ ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በ2015 መጨረሻ ዓመት መውጫ ፈተና በሁሉም መደበኛ እና መደበኛ ባልሆኑ መርሐ-ግብሮች የሚመረቁ ተማሪዎችን እንደሚመለከት እና ፈተናውን በኦንላይን ለመስጠት ዝግጅት እየተደረገ መሆኑን የትምህርት ሚኒስቴር ዴኤታ ዶክተር ሳሙኤል ክፍሌ ገልጸዋል።

የዩኒቨርሲቲ መውጫ ፈተና ከመደበኛ ተማሪዎች ባሻገር የማታ እና የርቀት ተመራቂ ተማሪዎችን እንደሚመለከትም ገልጸዋል።

ዶክተር ሳሙኤል ክፍሌ በመውጫ ፈተና ዙሪያ ለመንግሥት እና ለግል ዩኒቨርሲቲዎች የተዘጋጀ የምክክር መድረክ ላይ እንደገለጹት፣ መውጫ ፈተና በሁሉም ዩኒቨርሲቲዎች ለሚማሩ የቀን፣ የማታና የርቀት መርሐ-ግብር ተመራቂዎች ይሰጣል።

ከዚህ ዓመት ጀምሮ በመንግሥት እና የግል ዩኒቨርሲቲዎች ተግባራዊ የሚደረገውን የመውጫ ፈተና በኦንላይን ለመስጠት መታቀዱንም ጠቁመዋል።

በመሆኑም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማቱ የመሠረተ ልማት አቅሞቻቸውን ከወዲሁ በማረጋገጥ ለፈተናው ተገቢውን ዝግጅት እንዲያደርጉ ሚኒስትር ዴኤታው አሳስበዋል።

የከፍተኛ ትምህርት አካዳሚክ ጉዳዮች መሪ ሥራ አስፈጻሚ ዶክተር ኤባ ሚጀና በበኩላቸው፣ የመውጫ ፈተና የትምህርት ጥራትን ከማስጠበቅ ባሻገር የተማሪዎችን እና የተቋማቱን ብቃት ለማሳደግ እንደሚያስችል ጠቁመዋል።

በምክክር መድረኩ በመውጫ ፈተና ዙሪያ እየተደረገ ያለው ቅድመ ዝግጅት፣ የመሠረተ ልማት እና የ2015 ምሩቃን መረጃዎች ቀርበው ውይይት መደረጉን ከትምህርት ሚኒስቴር ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

# የትግራይ ታጣቂዎች ትጥቅ የሚፈቱበትን...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

የባለሙያዎች የጋራ ኮሚቴ ከትናንት ኅዳር 21 ቀን ጀምሮ ሽሬ ላይ ሥራውን መጀመሩን አገልግሎቱ ትናንት በሰጠው መግለጫ አስታውቋል።

ከፌዴራል መንግሥት እና ከትግራይ ታጣቂዎች የተውጣጣው የባለሙያዎች የጋራ ኮሚቴ በቀጣይ ጥቂት ቀናት ሥራውን ያጠናቅቃል ተብሎ እንደሚታመንም ገልጿል።

ኮሚቴው የሚያወጣው ዝርዝር ዕቅድ ትጥቅ የማስፈታት፣ ካምፕ የማስገባት እና ተያያዥ ጉዳዮችን የሚመልስ ይሆናል ብሏል የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ባወጣው ወቅታዊ መግለጫ።

ዝርዝር ዕቅዱን የማውጣት ተግባሩ፣ በቴክኒክ ጉዳዮች ምክንያት መዘግየቱን አገልግሎቱ ገልጿል።

በፌዴራል መንግስትና በሕወሓት መካከል የተደረሰውን የሰላም ስምምነት ተከትሎ በተለይ በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል በግጭት የተጎዱ የትግራይ፣ አማራና አፋር አካባቢዎች የሰብአዊ ድጋፍ እንዲደርስ በማድረግ ረገድ በመንግስትና በሰብዓዊ ድጋፍ ሰጪ አካላት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት እየተሠራ መሆኑም ይታወቃል። በፌደራል መንግስትና በሕወሓት መካከል በአፍሪካ ህብረት አደራዳሪነት የተደረገው የሰላም ስምምነት ተግባራዊ ለማድረግም መንግስት ቁርጠኝነቱን ሲገልጽ መቆየቱ የሚታወስ ነው፡፡

# የጉባኤው ከሁሉም ዓለም ጥግ በመጡ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

እንደተናገሩት፤ ጉባኤው ኢትዮጵያ እንዳይካሄድ ሰፊ ቅስቀሳዎች ቢካሄዱም በኢትዮጵያና አጋሮቿ በተደረገ ትልቅ ትንቅንቅ ጉባኤው በሀገሪቷ ላይ ከሁሉም የዓለም ጥግ በመጡ እንግዶች ተሳትፎ መካሄድ መቻሉ ለኢትዮጵያ ትልቅ ድል ነው።

እንደ ሚኒስትሩ ገለፃ፤ ኢትዮጵያ ላለፉት ጥቂት አመታት እያለፈችበት ያለው ሁኔታ ከባድ ቢሆንም ያንን እንደ መልካም አጋጣሚ በመቁጠር 17ኛው ዓለማቀፍ የበይነመረብ አስተዳደር ጉባዔ እዚህ እንዳይካሄድ በርካታ ዘመቻዎች ነበሩ። ኢትዮጵያም በዘመቻዎቹ ክብደት ሳትደናቀፍ ጉባኤውን በመዲናዋ አዲስ አበባ ማካሄዷ አሸናፊ ያደርጋታል።

ከኮሞሮስ እንዲሁም የኦሺኒያ ከተባሉ የደሴት ሀገራት ሁሉ ሳይቀሩ ኢትዮጵያ ላይ እንግዶች በጉባኤው ለመሳተፍ መምጣታቸውን የተናገሩት ዶክተር በለጠ፤ ኢትዮጵያም እንግዶቿን የተለያዩ መልካም አቀባበሎችን በማድረግ ሀገሪቷንም በበጎ የማስተዋወቅ ተግባር መከወኑንም ተናግረዋል።

ከተለያዩ የዓለም ጫፎች እንግዶች መጥተው ጉባኤውን መሳተፋቸውን ረጅም ርቀትን በመጓዝ ለመጡ እንግዶች የሚመጥን መርሀ ግብር መከወኑንም ዶክተር በለጠ አመላክተዋል።

እንግዶቹ ከያሉበት ሀገር ለጉባኤው ኢትዮጵያ ከመጡ በኋላ ባዩት ነገሮች ስለተሰማቸው ስሜት አስተያየት መጠየቃቸውን እና በምላሻቸውም ደስተኞች መሆናቸውን መግለፃቸውን የተናገሩት ዶክተር በለጠ፤ የሀገራት ተወካዮች እንዲሁም ታላላቅ የተቋማት ኃላፊዎችም ጭምር በየመድረኩ በተደረጉ ውይይቶች ኢትዮጵያን ማመስገናቸውንም ገልጸዋል።

ባሳለፍነው ሰኔ ወር ላይ በየአራት አመቱ የሚከወን የዓለማቀፍ የቴሌኮሙኒኬሽን ልማት ኮንፍረንስን ለማዘጋጀት ኢትዮጵያ እድል ተሰጥቷት ለሁለት ዓመት ሀገራዊ ዝግጅት ብታደርግም በብዙ ጫና እንዲሁም ሀገሪቱ በነበረችበት አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ምክንያት ከኢትዮጵያ ተነስቶ ለሩዋንዳ መሰጠቱን ዶክተር በለጠ ጠቁመው፤ ኢትዮጵያ ያንን ኮንፍረንስ ለማዘጋጀት ሙሉ አቅምና ዝግጅት አድርጋ ነበርና ኮንፍረንሱን መከወን ብትችል ኖሮ ብዙ እድሎችን ማግኘት ትችል እንደነበር በቁጭት ገልጸዋል።

የአሁኑንም ጉባኤ ኢትዮጵያ ላይ ለማካሄድ የተኬደው ሩጫ ቀላል እንዳልነበርና ኢትዮጵያ ጉባኤውን ማዘጋጀት ይበዛባታል በማለት እንዳይዘጋጅ ሲመክሩ በነበሩ አካላት ፊት ቀና ብላ እንድትታይና ታላቅ ድል እንድትቀዳጅ ያደረገ ትልቅ ገጠመኝ መሆኑን ዶክተር በለጠ ተናግረዋል።

ካሳለፍነው ሰኞ ህዳር 19 እስከ ህዳር 23 ቀን 2015 ዓ.ም ቆይታውን ያደረገው 17ኛው ዓለም አቀፍ የበይነ መረብ አስተዳደር ጉባኤ ዛሬ በአምስተኛ ቀኑ ፍፃሜውን እንደሚያገኝ ይጠበቃል።

# ከሱዳን ግዛት በመነሳት በኢትዮጵያ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ላይ ጥቃት ለመፈፀም የሚሞክሩ አካላትን ሱዳን እንደማትታገስም አረጋግጠዋል።

ከድንበር ጋር በተያያዘ የሚፈጠሩ ችግሮችን በኃይል ለመፍታት የሚደረግ ሙከራ ዘላቂ መፍትሄን የማያመጣ በመሆኑ ቀደም ሲል ሁለቱ ሀገሮች በፈረሟቸው ስምምነቶች አማካኝነት በሁለትዮሽ መስመር ለመፍታት ከመግባባት መደረሱም ተመላክቷል፡፡

የዓባይ ግድብን በተመለከተ በሱዳንና ኢትዮጵያ መካከል እየታየ ያለ በጎ የትብብር መንፈስ ልዩነቱን በሦስትዮሽ መንገድ ለመፍታት ለሚደረገው ጥረት አዎንታዊ አስተዋጽኦ እንዳለውም እምነታቸውን ገልፀዋል።

ጄነራል አብዱልፈታህ አልቡርሃን እና አቶ ደመቀ በድንበር አካባቢ የሚስተዋሉ ህገወጥ የሰዎች፣ የጦር መሳሪያ እና የአደንዛዥ ዕፅ ዝውውር በጋራ ለመከላከል ተስማምተዋል።

አቶ ደመቀ ቀደም ብለው ከሱዳን ሉዓላዊ የሽግግር ምክር ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት ጀኔራል መሀመድ ሀምዳን ደግሎ እና ተጠባባቂ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አሊ አል-ሳዲቅ ጋርም ተወያይተዋል።

በዚሁ ወቅት አቶ ደመቀ በሁለቱ ሀገራት የህዝብ ለህዝብ ትስስር እንዲጠናከር ትኩረት ተሰጥቶ መሰራት እንዳለበት አጽንኦት ሰጥተዋል፡፡

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ደመቀ በሱዳን ርዕሰ መዲና ካርቱም በተካሄደው የኢጋድ የሚኒስትሮች መደበኛ ስብሰባ መሳተፋቸው ይታወቃል።

የሱዳን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አሊ በበኩላቸው፤ በኢትዮጵያ መንግስትና ሕወሓት መካከል የሰላም ስምምነት በመፈረሙ ሱዳን መደሰቷን ገልፀው፤ ተግባራዊነቱን ሀገራቸው እንደምትደግፍና አዎንታዊ ሚና እንደምትጫወት አስታውቀዋል።

ሰላም ከሌለ ልማት የማይታሰብ በመሆኑ የኢትዮጵያ ሰላም የሱዳን ሰላም እንደሆነም ጠቅሰዋል።

በካርቱም የተካሄደው የኢጋድ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ስብሰባ እንዲሳካ ኢትዮጵያ ላዳረገችው አስተዋጽኦ እና ላሳየችው አጋርነት ማመስገናቸውን የዘገበው ኤፍቢሲ ነው፡፡

# ከ70 ሺ ሜትሪክ ቶን በላይ ምግብና...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

በላይ ማጓጓዝ ተችሏል። ይህ የተላለፈው በአብአላ እና በሽሬ መንገድ ነው። ይህ የሚያሳየው ሁሉም አይነት ድጋፎች አለምንም ገደብ ለተጠቃሚው ማኅበረሰብ እንዲደርሱ የማድረግ ስራ እየተከናወነ መሆኑን ነው ሲሉ አስረድተዋል።

ከስምምነቱ በኋላ ወደ አራት ኮሪደሮችን በመለየት ስራው እየተሰራ እንደሆነ የጠቀሱት አምባሳደር ሽፈራው፤ የመጀመሪያ የእርዳታ ድጋፉ ማስገቢያ ኮሪደር በአፋር ሰመራ በኩል ያለ የሰመራ አብአላ ኮሪደር ሲሆን፣ በዛ በኩል በአብዛኛው ወደ መቀሌ የሚደርሱ ድጋፎች የሚተላለፉበት መንገድ ነው ብለዋል። ሁለተኛው በሰሜን ወሎ በወልዲያ አድርጎ በአላማጣ ኮረም በኩል የሚሄደው ሲሆን፣ እሱም በአማራ አካባቢ የግጭቱ ሰለባ የሆኑትን ጨምሮ የሚያዳርስ መንገድ ነው። ሶስተኛው በሰሜን ጎንደር ደባርቅ አድርጎ በአደይ አርቃይ፣ ማይጸብሪ እስከ ሽሬ ድረስ የሚሄድ መስመር ሲሆን፣ በዚህ መስመርም በየብስ የሚጓዙ ተሽከርካሪዎች ድጋፍ እያደረሱ እንደሚገኙ ገልጸዋል። አራተኛው የጎንደር ሁመራ መስመር ሲሆን፣ ከሁመራ ሽራሮ፣ ሽሬ፣ አክሱም፣ አድዋ እያደረገ በየመሃሉ ያሉ ሁሉንም ከተሞችና አካባቢዎችን በሚሸፍን ሁኔታ የሚሄድ እንደሆነ አምባሳደር ሽፈራው አመልክተዋል።

ይህ ድጋፍ በየብስ የሚሰራው እንደተጠበቀ ሆኖ በአየርም ጭምር እየተደገፈና እየተከናወነ የሚገኝ ነው። በአሁኑ ወቅት ወደ ሽሬ ሁሉም አይነት ቁሳቁስ፣ መድሃኒት እንዲሁም የተወሰኑ ሌሎች ቁሳቁስም ይጓጓዛሉ። ወደ መቀሌም በተመሳሳይ ገንዘብና መድኃኒትን ጨምሮ በመጓጓዝ ላይ ይገኛል። ስለዚህ ያለገደብ ሊኖር ይገባል የተባለው የሰብዓዊ ድጋፍ ስራዎች በአራቱ መስመርና የአየር መንገድ መስመሮች እየተከናወኑ ናቸው ብለዋል።

ዶክተር ሽፈራው እንደተናገሩት፤ እዚያ ለሚያገለግሉ የተለያዩ ሰራተኞችም እስከ ዛሬ ባለው ስሌት የተላለፈው ገንዘብ መጠን ወደ 150 ሚሊዮን ብር ነው። ይህ ትግራይ ውስጥ ላሉ ሰራተኞች ደመወዝ፣ ስራ ማስኬጃቸው እንዲሁም ለአንዳንድ የመጫንና የማውረድ ስራዎች ለክፍያ የሚውል ነው።

ከ70 ሺ ሜትሪክ ቶን በላይ የተባለው እህል በ15 ኪሎ ግራም ሲሰላ ምን ያህል ማኅበረሰብ ሊያዳርስ ይችላል ከተባለ በቀላሉ ከአምስት ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ሊያዳርስ የሚችል ነው ያሉት አምባሳደር ሽፈራው፣ ይህ የመድሃኒቱም የነዳጁም ሌሎች ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁስን ሳይጨምር ነው ብለዋል። ይህ የሚያሳየው ሰፊ የሆነ የመንግስት አቅም ቀድሞ ጀምሮ እንደነበረና ኋላ ላይ ደግሞ አጋር ድርጅቶችም የሰብዓዊ ድጋፍ የሚሰጡ ድርጅቶችም አቅማቸውን እያጠናከሩ መሄዳቸውን እንደቀጠሉ የሚያመላክት መሆኑን ተናግረዋል፤ በአሁኑ ወቅት ከአንድ ሺ 100 ትልልቅና ከባድ ተሳቢ የጭነት ተሽከርካሪዎች በላይ ወደስፍራው በመግባት ድጋፉን በማድረስ ላይ እንደሚገኙም ተናግረዋል።

እንደ ኮሚሽነር ሽፈራው ገለጻ፤ አጋር የሚባሉ ብዙ ናቸው፤ እስካሁን ባለው ላይ የተሳተፉት ወደ 16 የሚጠጉ ናቸው። ስራቸውን የሚሰሩት በተለያየ ሁኔታ ሲሆን፣ ለአብነትም ድጋፉን በገንዘብ የሚያግዝ አለ፤ ይህ አጋር ገንዘብ ለጋሽ የሚባለው ነው። ያንን የገንዘብ ድጋፍ ተከትሎ ተግባሩን ደግሞ የሚፈጽም አካል አለ። ከዛ አካል ይቀበልና መሬት ላይ ያለውን የማሰራጨት እንዲሁም የማስተዳደር ስራ የሚሰራ አለ።

መታወቅ ያለበት ጉዳይ ትልቁ ተዋናይ መንግስት መሆኑ ነው ያሉት አምባሳደሩ፤ ከእሱ ቀጥሎ ደግሞ ሁለት ትልልቅ ተቋማት መኖራቸውን ጠቅሰው፤ እነርሱም ሲ.አር.ኤስ ጆብ (የካቶሊክ ሪሊፍ ሰርቪስ) የሚባል የተለያዩ ተቋማትን ይዞ የሚሰራ አንዱ ነው ብለዋል። ሌላው የዓለም ምግብ ፕሮግራም (ደብሊው.ኤፍ.ፒ) የሚባል መሆኑን ገልጸዋል።

አምባሳደር ሽፈራው፣ በመንግስት መሪነት የተጀመረው የድጋፍ ስራው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ጠቅሰው፤ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ግን ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ ይገባል ብለዋል። ሁሉም በተቻለው መጠን መንግስትም አጋር ድርጅቶችም ዳያስፖራውም ሆነ ማኅበረሰባችንም ራሱ የሚችለውን እያደረገ ከሄደ ሁላችንም የምንመኘው ሰላምና ከሰላሙ የምናገኘውን የተለያዩ ትሩፋቶች ልናጣጥም እንችላለን በማለት ተናግረዋል። በዚህ ውስጥ ከመሳተፍና የዚህ አካል ከመሆን ማንም ሰው መቆጠብም መገደብም እንደሌለበት አመልክተው፤ ሁላችንም ተረባርበን መስራት ይጠበቅብናል ብለዋል።

ማህበራዊ

# ሀገርኛ

# አገር በቀል ተቋማትና እሴትን የማስቀጠል ተግባራቸው

ግርማ መንግሥቴ

በአገራችን ታሪክም ሆነ ቱባ ባህል መሰረት የታረዘን ማልበስ፣ የተራበን ማብላት፣ በአጠቃላይ በተለያዩ ችግሮች ውስጥ የሚገኙ ወገኖችን "ከጎናችሁ ነን! አለንላችሁ! አይዟችሁ!" ማለት የእኛ፣ የኢትዮጵያዊያን ቱባ እሴት ነው።

ይህን ዓይነቱ ታሪክ፣ ባህል …፣ ባጠቃላይ እሴት ትውልድ በቅብብሎሽ ይዞት እንዲቀጥልና እንዲያስቀጥል የሚጠበቅ ሲሆን፤ ምንም እንኳን መሀል ላይ የተዳከመ መስሎ ብዙዎችን አሳስቦ የነበረ ቢሆንም፣ የበለጠ ተጠናክሮ በመቀጠል ላይ ይገኛል፡፡ ይህንን መሬት ለማስያዝ በርካታ ማሳያዎች ያሉ ሲሆን፣ የማዕድ ማጋራት፣ የአልባሳት፣ የገንዘብና የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች ወዘተ ድጋፍ ማድረግ፤ ከሰራዊቱ ጎን ሳይቀር የመሰለፍና ድጋፍ ማድረግ … እና የመሳሰሉት ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው፡፡ በተለይ "ሰውን ለመርዳት ሰው መሆን ብቻ በቂ ነው" (ይህ መርህ እንደ አንድ ሰብዓዊ መርህ ተወስዶ በመጀመሪያ ሲቀነቀን የሰማሁት በፕሮፌሰር መስፍን ወልደማሪያም ነው) የሚለው አስተሳሰብ እየሰረፀ መምጣቱ በራሱ አንድ ትልቅ እርምጃ ነውና የአሁኑም ሆነ መጪዎቹ ትውልዶች ይህ ቋሚ መርሀቸው እንደሚሆን ይጠበቃል።

በ2001 ዓ.ም የወጣው የበጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ኤጀንሲ ሕግ በ2012 ዓ.ም እስኪሻሻል ድረስ ባለው ግዜ ውስጥ ማህበራት፣ በጎ አድራጎት ድርጅቶችና የሰብዓዊ መብት ተሟጋች ተቋማት ፈርሰዋል፤ አልያም በእጅጉ ተዳከመዋል … የተባለበት ወቅት ሲሆን፤ ከህጉ መሻሻልና "የኢፌዴሪ በጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ማህበራት ኤጀንሲ" መቋቋም በኋላ በተሻለ ሁኔታ ዘርፉ እየተጠናከረ መምጣቱ ይነገራል። የሚመለከታቸው ተቋማት መረጃዎችም የሚያሳዩት ይህንኑ ነው።

በተለይ "ሰውን ለመርዳት ሰው መሆን ብቻ በቂ ነው" የሚለው ሀሳብም ይሁን አስተሳሰብ ምንም የማይወጣለት፤ ፍፁም ሰብዓዊና ሰው ተኮር እንደ መሆኑ መጠን በመርህነት መያዙና በሱም ጥላ ስር መሰባሰቡ በየትኛውም መስፈርት ተገቢነት ስላለው ተጠናክሮ ቢቀጥል እንጂ የሚዳከም ጉዳይ አይደለም። ሜቄዶኒያን የመሳሰሉት ተቋማት መርሀቸው ይኸው በመሆኑም በመርሁ እየተመሩ፤ የበለጠም እየተጠናከሩና ተደራሽ እየሆኑ ዘለቁ እንጂ የተቀዛቀዙበት ጊዜ አልታየምና መርሁ አሰሪም አዋጭም ነው። ዳር ዳርታችን ወደ "በጎ አድራጎት"፤ በተለይም "አገር በቀል በጎ አድራጎት ድርጅቶች" ነውና ወደዛው እንሂድ።

እንደሚታወቀው፣ አገር በቀል ተቋማት፣ የማህበረሰቡ አካል እንደመሆናቸው መጠን፣ ስነልቦናን በመረዳት፣ ባህልና የአኗኗር ዘይቤን በማክበር፣ እንዲሁም በወገንተኝነትና ተቋርቋሪነት ስሜት ሊሰሩ መቻላቸው አገርን ለማሻገርና ማህበረሰብን ለማንቃት የሚኖራቸው ሚናም ሆነ ድርሻ ከፍተኛ ነው፡፡

ዲሞክራሲን ለመተግበር፣ ሰብዓዊ መብቶችን ለማክበርና ለማስከበር እንዲሁም ለሕግ ተገዥ የሆነ ማህበረሰብን ለመፍጠር ሕጎችና ፖሊሲዎችን ከማጽደቅና ለመተገበር ከመስራት ባለፈ፣ መርሆቹ የማህበረሰብ ባህልና አስተሳሰብ እንዲሆኑና በየእለት ሕይወት ውስጥ እንዲተገበሩ መስራት ግድ ይላል፡፡ በበርካታ አገራት እንደታየው ይህንን ንቃተ ህሊና መፍጠር ደግሞ በዋነኛነት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ሚና ከፍተኛና ከዚህ መለስ የሚባል አይደለም፡፡ የዜጎችን ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ሥነ ልቦናዊ በደል ከመታደግ አኳያም እንደዛው። (ለምሳሌ፣ የዛሬን አያድርገው እንጂ እነ አምነስቲ ከፈጣሪ በታች የሚታመኑም የሚመለኩም ይሆኑ ዘንድ አስችሏቸው የነበረው ይህ ተግባራቸው ነበር።)

እዚህ ላይ አንድ ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚያስፈልገው መሰረታዊ ጉዳይ ቢኖር "ምን አይነት ሰው መፍጠር ነው ከእነዚህ ድርጅቶች የሚጠበቀው?" የሚለው ነው። እንደ ባለሙያዎችም ሆነ ዓለም አቀፍ ጥናቶች አተያይ አንድ ድርጅት ዝም ብሎ ብቻ እርዳታ መስጠትና መቀበል ላይ ማተኮር የለበትም። የተቋማቱ ትኩረት ይህ ከሆነ የተረጂነት መንፈስ ሥር ሰዶ ይንሰራፋል፡፡ እንደ ባህልም ይዳብራል፡፡ ከዳበረና ሥር ከሰደደ በኋላ ደግሞ ለመመለስና ለማስተካከል ፈታኝ ይሆናል፡፡ ሥራ ፈጣሪ ትውልድ መተካት ሲገባው ሁልጊዜ የዕርዳታ እጅ የሚጠባበቅ ዜጋ ሆኖ ይቀራል፡፡ በመሆኑም ይህ እንዳይሆን ከፍተኛ ጥንቃቄን ይፈልጋል ማለት ነው።

መልካምነት የበጎ አድራጎት ማ/ር

CHARITY GROUP

በአንድ ወቅት የተረጂነትን መንፈስ ለማስወገድ አቅም በፈቀደ መጠን ከሚንቀሳቀሱ ተቋማት መካከል "ጳጉሜን አምስት ግብረ ሠናይ ድርጅት" ያከናወናቸው ተግባራት ለአብነት ይጠቀሳሉ፡፡

የድርጅቱ መሥራችና ሥራ አስኪያጅ አቶ ኤርሚያስ ገሠሠ እንደገለጹት፣ በቦሌ ክፍለ ከተማ ወረዳ 14 ከሚገኙት ችግረኞች መካከል አቅም በፈቀደ መጠን 150 ያህሉን ከተረጂነት ለማላቀቅ የሚያስችል ፕሮጀክት ተቀርፆ ለተግባራዊነቱ እየተንቀሳቀሱ መሆናቸውን የሚናገሩ የሚዲያ ዘገባዎች ስንሰማ እንደነበር እናስታውሳለን።

ስራ አስኪያጁ "የጎዳና ሕይወትን የሚኖሩ፣ ቀን ጨልሞባቸው ለተለያዩ ችግሮች የተጋለጡ … እነዚህን ወገኖች ከተረጂነት የማላቀቁ ሥራ የሚከናወነው በኮንስትራክሽንና በጨርቃ ጨርቅ (ጋርመንት) ሥራዎች ላይ በማሰማራት መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ለዚህም ዕውን መሆን ሁኔታዎች መመቻቸታቸውንና በሚሰማሩባቸው የሥራ መስኮች ላይ ያተኮረ ሥልጠና እንደተሰጣቸው፣ በሥልጠናውም ያገኙትን ዕውቀት የማጠናከር ሥራ ላይ ያተኮረ ሌላ ሥልጠናም በቅርቡ እንደሚሰጣቸው" መናገራቸውም እንደዚሁ በተያያዘ ዜና (ሴፕቴምበር 14 ቀን 2022) መነገሩ አይዘነጋም።

የዚህ ምክንያቱ ደግሞ ከላይ ያልነውን፣ የተረጅነትና ጠባቂነት መንፈስ እንዳይሰፍን ለማድረግ ከማሰብ የመጣ ነውና ሁሉም ይህንኑ ጉዳይ ሊያስቡበት ይገባል ማለት ይሆናል።

ተቋማቱ ከእርዳታና ድጋፍ፣ ልገሳና ረድኤት ባለፈ ከሰላምና ፀጥታ … አኳያም የሚጫወቱት ሚና ቀላል አይደለም። ብሔርና ኃይማኖት ተኮር ግጭቶችን በምታስተናግደው ናይጄሪያ፣ ነገሮች ከቁጥጥር ውጭ እንዳይሆኑ በመንግስት የሚደርገውን ጥረት በማገዝ፣ የተጋጩ ወገኖችን ለንግግር በመጋበዝና በማሸማገል ረገድ በጎ አድራጎት ድርጅቶች ቁልፍ ሚና ሲጫወቱ መቆየታቸው፤ አሁንም በመጫወት ላይ መሆናቸው ይታወቃል፡፡

ከእርስ በርስ ጦርነት፣ ከዘር ማጥፋትና ከዘረኝነት ግጭቶች ተላቀው አገር ለማስቀጠል በቻሉት እንደ ሩዋንዳና ደቡብ አፍሪካን የመሳሰሉ አገራትም በተለይ አገር በቀል ተቋማት ያደረጉት አስተዋጽኦ ዘርፉን ከማጠናከርና የሚጫወተውን ጉልህ ሚና ከማስቀጠል አኳያ ተደጋግመው የሚጠቀሱ እንቅስቃሴዎች ናቸው፡፡

እነዚህ ተቋማት፣ የአገር ውስጥም ሆኑ የውጭ፣ ከፖለቲካ ነጻ እንደመሆናቸው መጠን፣ የሚኖራቸው ተአማኒነት፣ ተቀባይነትና ማህበረሰብ ጋ የመድረስ፤ ማህበራዊ አገልግሎት የመስጠት ጉልበታቸው በቀላሉ የሚታይ አይደለም። ይህ ሁሉ ግንዛቤ ውስጥ ገብቶ ነው እንግዲህ በአዋጅ ተደግፈው፣ ደንብና መመሪያ ወጥቶላቸው ወደ ስራ እንዲገቡና የአገርና ትውልድ የማስቀጠል ሀላፊነታቸውን እንዲወጡ የተደረገው።

እርግጥ ነው፣ አንዳንድ አገር በቀል የሆኑትም ሆኑ ያልሆኑት፣ ከተቋቋሙበትም አላማም ሆነ ደንብና ስርአት ውጭ በመሆን በተቀራኒው የሚሰሩ አሉ። ይህ ደግሞ ሁሌም የሚታይና የሚሰማ ሮሮና ንቅዘት ስለሆነ እዚህ መድገሙ አያስፈልግም። ምናልባት ስለ ጉዳዩ ሰፋ አድርጎ መመልከት ለፈለገ ግን ከብዙዎቹ አንዱ የሆነውን፤ "ሪፖርተር" ጋዜጣ የካቲት 25 ቀን 2010 ዓ.ም፣ በገጽ 42 ላይ «የችግሩ ሰለባ የሆኑ ዜጎች የመፍትሔው አካል ይደረጉ፤» በሚል ርዕስ ያቀረበውን ጽሑፍ፤ እንዲሁም፣ እሱን ተከትለው ለንባብ የበቁ (ለምሳሌ "የበጎ አድራጎት ድርጅት ሠራተኞችም ተመልካች ይሻሉ" በሚል ርእስ የቀረበው) አስተያየቶችን መመልከት የሚቻል ሲሆን፤ እየተነጋገርንበት ላለው ጉዳይም ጥሩ ማሳያዎች ናቸው። ወደ ዛሬው ጽሑፋችን መነሻ ወደ ሆነው "መልካምነት የበጎ አድራጎት ማህበር" እንምጣ።

"መልካምነት የበጎ አድራጎት ማህበር" በ2012 ዓ.ም በ55 ተማሪዎች አማካኝነት የተመሰረተ፣ ታዳጊ ማህበር ሲሆን የማህበሩ መቀመጫም ከአዲስ አበባ 120 ኪ.ሜ ርቀት ላይ በምትገኘው አምቦ ከተማ ነው።

ከማህበሩ መስራችና ሊቀ መንበር ወጣት ዳግም ገዛኸኝ ጋር ባደረግነው ቆይታ እንዳጫወተን ከሆነ ለማህበሩ መመስረት ዋና ምክንያት የሆነው በአካባቢው አቅመ ደካሞችና ርዳታ ፈላጊ ወገኖች፤ መማር እየተገባቸው መማር ያልቻሉ ህፃናትና ወጣቶች መኖር፤ እንዲሁም ምንም አይነት ገቢና ረዳት የሌላቸውና በከፋ ችግር ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች መኖራቸውና እነሱን መደገፍ የዜግነት ብቻ ሳይሆን፤ ሰው የመሆን ግዴታም ጭምር መሆኑ ነው።

ከአምቦ አስተዳደር እውቅና አግኝተን፣ ሰርተፊኬትም ተሰጥቶን በመንቀሳቀስ ላይ ነን የሚለው ሊቀመንበር ዳግም ከህብረተሰቡ በኩል በከፍተኛ ደረጃ እነዚህን ወገኖች የመርዳት ፍላጎት እንዳለ፤ በመኖሩም እነሱ በጠየቁ ቁጥር ከግለሰቦች ጀምሮ እስከ ተቋማት ድረስ እንደሚተባበሯቸውና ያላቸውን እንደሚለግሱ፤ "መልካምነት የበጎ አድራጎት ማህበር"ም ያሰባሰበውን ሀብት ለሚመለከታቸው ተደጓሚዎች እንደሚያደርስ ይናገራል።

አባላቶቻችን ትምህርታቸውን አጠናቅቀው ወደ ተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች በመሄዳቸው ምክንያት የአባላቶቹ ቁጥር በጣም ቀንሶ 25 ደርሷል። ይህንን የአባላት ቁጥር ከፍ ለማድረግ እየሰራን ነው ያለን ወጣት ዳግም የአካባቢው ወጣት ተሳትፎ የሚደነቅና ተጠናክሮ ሊቀጥል የሚገባ መሆኑንም ይገልፃል። በወጣቱ ከሚያደርጉት ተሳትፎዎች በተጨማሪ ወደ እነሱ ማህበርም በመምጣት አባል እንደሚሆኑም ተስፋ እንዳለው ይናገራል። በማህበሩ ድረ ገፅም ላይም ይኸው ሰፍሮ ለንባብ በቅቷል።

"ሰው ነንና ሰውን እንርዳ!!!" በሚል መርህ የሚመራው መልካምነት የበጎ አድራጎት ማህበር ከዚህ በፊት በተለያዩ ዙሮች ለተቸገሩና አቅም ለሌላቸው አረጋዊያን የቤት አስቤዛ ሲያድል እንደቆየው ሁሉ፣ ባለፈው ፋሲካም 5ኛውን ዙር እርዳታ የማሰባሰብ ተግባር ("ለበዓል ለ16 ቤተሰቦች አስቤዛ ለማስገባት 50ሺህ ብር" እንደሚያስፈልገው በመግለፅ) ፈፅሞ "የወር አስቤዛ (ጤፍ፣ ዘይት፣ ስኳር እና ሽንኩርት) በተለያዩ ጊዜያት ሰጥተናል።" በማለት በማህበራዊ ድረ-ገፁ ለአባላቱና ደጋፊዎቹ ይፋ አድርጓል። በተለያዩ ጊዜያትና በዓላት "የምገባ ፕሮግራም" ማካሄዱንም በፎቶግራፍ አስደግፎ ገፁ ላይ አስፍሯል። ከወጣት ዳግም ገዛኸኝም ይህንኑ አረጋግጦልናል።

ይህ አገር በቀል ድርጅት በወጣቶች የሚመራ ሲሆን የሚያከናውናቸውን አበይት ተግባራትን በተመለከተ የማህበሩ ሊቀመንበር የሆነው ዳግም ገዛኸኝ "የምንሰራቸው ስራዎች - የወር አስቤዛ መሸፈን፤ የአልባሳት ድጋፍ" ማድረግ በማለት የሚገልፃቸው ሲሆን፤ ከገቢ ምንጮቹ ጥቂቶቹን ሲገልፅም "ሊስትሮ በመስራት እንዲሁም ፌስ ማከስ በመሸጥ፤ ኩፖን በመሸጥ፤ 'string art' (በተለያዩ ቁሶች የተለያዩ ሥዕሎችን በመሣል) በማዘጋጀትና በመሸጥ እንደሆነ ይናገራል። "በተለያየ መንገድ እጃችሁን እንድትዘረጉልን በአክብሮት እንጠይቃለን። የእጅ ጌጥ በምትፈልጉትን ስም በማሰራት (በመግዛትም ጭምር) አንድም ይጠቀሙ፤ እግረ መንገድዎትንም የተቸገሩትን ያግዙ …." ሲልም ጥሪ ያቀርባል። በአብዛኛው ከእርዳታ ሰጪ ግለሰቦች ለድጋፍ የሚሆነውን ገንዘብ እንደሚያገኙ ነግሮናል።" የቤት እድሳት የምናካሄድበት እለትም አለ ሲልም የሚከናወኑ ተግባራትን ፕሮግራሞች በቦታና ጊዜ ለአባላትና ባለድርሻ አካላት እንደሚገለፅ ይናገራል።

ይህ "መልካም እናድርግ መልካምነት ኃይማኖት፣ ብሔር … አይገድበውም። ፈጣሪን መውደዳችንን ሰዎችን በመርዳት እናስመስክር። ሰው ነንና ሰውን እንርዳ!!"ን መርሁ ያደረገው "መልካምነት የበጎ አድራጎት ማህበር" የተቸገሩ ወገኖችን ለመርዳት በዚህ እንደማይገደብና ወደፊት ሌሎች በርካታ ስራዎችን ለመስራት እቅድ እንዳለው ሊቀመንበሩ የተናገረ ሲሆን፤ ይህንንም "ወደፊት እቅዳችን ከአንድ ቤተሰብ ውስጥ አንድ ሰው ራሱን እንዲችል ማድረግ ነው። ከአንድ እርዳታ ከሚፈልግ ቤተሰብ ውስጥ በአንድ በሆነ መንገድ፣ ሙያ … ራሱን ችሎ ቤተሰቦቹንም እንዲያግዝ የማድረግ እቅድ ይዘን ነው እየተንቀሳቀስን ያለነው" በማለት ይገልጸዋል።" ይህም ይሳካልናል ብለን ተስፋ እናደርጋለን" ሲልም ያክላል።

"ከመስተዳድሩ ያገኛችሁት ድጋፍ ካለ?" ብለነውም "የአምቦ ከተማ መስተዳድር ከእውቅና መስጠት ጀምሮ ከጎናችን ነው። ስብሰባ የምናካሂደውም በወጣቶች ማእከል ነው። መስተዳድሩና ሌሎች አካላትም እንዲተባበሩን የጠየቅናቸው ጉዳዮች አሉ። እስካሁን ምላሽ ባናገኝም ወደፊት ምላሽ ይሰጡናል ብለን እንጠብቃለን።" ሲል ነው የገለፀልን።

በመጨረሻም "ለአንተና አንተን መሰል ወጣቶች በአጠቃላይ የምታስተላልፈው መልእክት ካለ?" ብለነውም "በየአካባቢው በጣም የተቸገሩ ሰዎች አሉ። ብዙ ሰው በከፋ ሁኔታ ውስጥ አለ። እያንዳንዳችን አካባቢያችንን ብንቃኝ ይህ ችግር ግልፅ ሆኖ ይታየናል። በመሆኑም ይህ ችግር በመንግስት ትከሻ ብቻ ይፈታል ተብሎ ማሰብ ስለማይቻል፤ ችግሩን ከመፍታትና ለእነዚህ ወገኖች ከመድረስ አኳያ ወጣቱ የራሱ የሆነ ሀላፊነት አለበት። በመሆኑም፣ ይህንን ሀላፊነቱን በውል በመረዳት በራሱ መንገድ፣ በመደራጀትም ይሁን በሌላ ለእነዚህ ወገኖች መድረስ አለበት።" በማለት የ"መልካምነት የበጎ አድራጎት ማህበር" የኮሌጅ ትምህርቱን ጨርሶ በግል ስራ ላይ የተሰማራው የ25 አመቱ ወጣትና የማህበሩ ሊቀመንበር ዳግም ገዛኸኝ መልሶልናል።

እኛም እንላለን፤ ቀደም ሲል በመግቢያችን ላይ ሰፋ አድርገን እንደገለፅነው ሁሉ፣ አገር በቀል ድርጅቶች ከአገር ውጭ ከመጡት በብዙ መልኩ የተሻሉና ተመራጭ ናቸው። ርእሳችንን "አገር በቀል ተቋማትና እሴትን የማስቀጠል ተግባራቸው" ብለን ስንነሳ በጎ አድራጊነት (በሌላ ስሙ "አገልጋይነት") እሴታችን መሆኑን መግለፃችን ነውና ወጣቶችም ሆኑ ሌላው ዜጋ በእንደዚህ አይነቱ በጎ አድራጎት ተግባራ ላይ ቢሰማራ አገርም፤ ወገንም ይጠቀማል፤ ቱባው የመረዳዳት፣ መተጋገዝ … እሴታችንም ይቀጥላል ብለን እናስባለን። የ"መልካምነት የበጎ አድራጎት ማህበር" አባላትንም በርቱ ስንል የሚመለከተው ሁሉ ይተባበራቸዋል ከሚል እምነት ጋር ነው።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

# ሰዋሰውን በ‹‹ሪቂቻ››

**አስናቀ ፀጋዬ**

ዶክተር ሐብታሙ ገበየሁ ትውልድና እድገቱ ጎንደር ገጠራማ አካባቢ ነው። ትምህርቱን በአዲስ አበባ ተከታትሏል። በቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ህክምና ኮሌጅም በህክምና ሙያ ያገለግላል። በቅርቡ ‹‹ሪቂቻ›› የተሰኘና የኦሮምኛ ቋንቋ ሰዋሰው ለጀማሪዎች መፅሃፍት አሳትሟል።

ዶክተር ሐብታሙ ይህን መፀሃፍ ያዘጋጀው በአጋጣሚ ነበር። ቋንቋን ማንም ሰው መናገር እንደሚፈልግ ሁሉ እርሱም ተጨማሪ ቋንቋዎችን የማወቅ ፍላጎት ነበረው። ጠቅላላ ሐኪም ከሆነ በኋላ በቂ ጊዜ ስለነበረው የተለያዩ መፅሃፎችን ያነብ ጀመር። ይህ የማንበብና ቋንቋን የማወቅ ፍላጎቱ በአንድ ነገር የበለጠ እንዲበረታ አስቻለው። ይህም የኦሮሚኛ ቋንቋን መናገር ነው። የቋንቋውን መዝገበ ቃላትና የንግግር መፅሃፍቶችን ማንበቡ ደግሞ ለዚህ አግዞታል።

ባለቤቱ የምታውቃቸው የተወሰኑ የኦሮሚኛ ቋንቋ ቃላት ነበሩ። እርሱም ባለው ጊዜ እርሷ የምታውቃቸውን ቃላት የማወቅና የመረዳት አጋጣሚ ተፈጠረለት። ከዛም በድረገፆች ላይ የቋንቋውን ቃላቶች በመፈለግ በርካታ የኦሮሚኛ ቃላትን ማወቅ ቻለ። በሂደት ብዙ ቃላትን አውቆ በመጨረሻ ቃላቱን ወደ አረፍተ ነገር መመስረት ከፍ አደረገው። በእርግጥ ይህንን ወዲያውኑ ማድረግ አልቻለም ነበር። ምክንያቱም የቋንቋውን የሰዋሰው ስርዓትና ትርጉም አያውቀውም።

ዶክተር ሀብታሙ ስህተቱ የቱ ላይ እንደተፈጠረ ሲረዳም ስህተቱን ለማረም እርሱ በሚያውቀው ቋንቋ በአማርኛና በእንግሊዘኛ የተዘጋጀ ሰዋሰው መፅሃፍ መፈለግ ጀመረ። ነገር ግን እንደዚህ አይነት መፅሃፍ ማግኘት አልቻለም። ይሁንና በዚህም ተስፋ አልቆረጠም። ይልቁንም ወደ ቋንቋ ትምህርት ቤት ሄዶ የኦሮሚኛ ቋንቋ ሰዋሰው ትምህርት ተማረ።

የሰዋሰው ቋንቋውን ትምህርት ቢጀምርም በኦሮምኛ ቋንቋ የተፃፈ የሰዋሰው መፅሃፍ ፍለጋውን ግን አላቆመም። ነገር ግን አሁንም ምንም ያገኘው ነገር አልነበረም። እናም እራሱ የመፍትሄ አካል ለማድረግ አሰበ። ትምህርቱን ሲከታተል ማስታወሻ በሚገባ እየያዘ ሲማር፣ ሰው ሲጠይቅ፣ መዝገበ ቃላትን ሲያነብና በኢንተርኔት ቋንቋውን ሲፈልግና የተረዳውን እየፃፈ ቆየ። በዚህም እያደር የቋንቋውን አካሄድ፣ ፍሰት ተረዳ።

የመዘገበው ማስታወሻ በሂደት ብዙ የሆነለት ዶክተር ሐብታሙ፤ እንደእርሱ አይነት ቋንቋውን መማር የሚፈልጉ ሰዎች የእርሱ አይነት ችግር እንዳይገጥማቸው ሲል ማስታወሻውን ወደመጸሐፍነት ቀየረው። በእርግጥም መጸሐፍ አለ ብሎ ቢፈልግም ስላላገኘ አማራጭ ይሆናል ብሎ አመነም። እንዳሰበውም ለብዙዎች ተስፋ ሆኗል።

ቋንቋን የማወቅ ፍላጎት የጀመረው ሥራ ከመጀመሩ በፊት ቢሆንም የሕክምና ባለሙያ ሆኖ በአቤት ሆስፒታል ሲቀጠር በሆስፒታሉ የሚመጡ አብዛኞዎቹ ታካሚዎች ከአዲስ አበባ ዙሪያ የሚመጡ የኦሮሚኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ነበሩ። ስለሆነም ከእነዚህ ታካሚዎች ጋር ለመግባባት አስተርጓሚዎችን ሁሌ መጠቀም ሰልችቶታል። በዚያ ላይ የተፈለገውን መረጃ ማግኘት ስለማይችል በሚፈልገው ልክ ሊረዳቸው አይችልምና ውስጡ ቋንቋውን እወቅ አለው።

ቋንቋውን የማወቅ ፍላጎቱ በብዙ ችግሮች ቢፈተንበትም እያየለበት የመጣውን ጉጉት መልቀቅ አልፈለገም። ስለዚህም መጀመሪያ መጸሐፍትን ማንበብ አልሆንልህ ሲለው ደግሞ ወደ ቋንቋ ትምህርት ቤት መግባትን መፍትሄ አድርጎ ወሰደ። ከዚያ ውጤቱን ሲያየው እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል ሳይል የነበረበትን ፈተና ፈትቶ ለሌሎች ተስፋ ለመሆንም ጣረ። ይህም የኦሮሚኛ ሰዋሰው መፅሃፍ ዝግጅት ነው።

ዶክተር ሀብታሙ የኦሮሚኛ ቋንቋ ትምህርቱን ከጀመረ ሦስት ዓመት ሆኖታል። ከዚያ በፊት ግን ስለኦሮሚኛ ቋንቋ ምንም ነገር አያውቅም። የ36 ሰዓት ኮርስ ወስዷል። የተማረውም ከሌሎች ተማሪዎች ጋር ሳይሆን በግሉ ነው። ለሁለት ዓመት ከቋንቋው




ጋር ከተዋወቀ በኋላ የያዛቸው ማስታወሻዎች ስለነበሩ የኦሮሚኛ ቋንቋ ሰዋሰው መፅሃፉን ለማዘጋጀት ብዙ ጊዜ አልፈጀበትም። በአንድ ዓመት ውስጥ ጽፎ ለንባብ አብቅቶታል።

ከማስታወሻዎቹና ከሌሎች ማጣቀሻ መፅሃፍቶች ያዘጋጀውን ባለ 264 ገፅ ጥራዝ አንድ ላይ በማድረግ ካጠናቀቀ በኋላ ራሱ የአርትኦት ሥራውንም ሰርቷል። የአሳታሚውን መብትም አስጠብቋል።

ቋንቋውን ገና የጀመረው እንደመሆኑ ስህተት ሊኖረው እንደሚችል አስቀድሞ በመገንዘብ አብረውት የተማሩና አፋቸውን በኦሮሚኛ ቋንቋ የፈቱ ሁለት ጓደኞቹ በአዘጋጀው ጥራዝ ላይ ተጨማሪ የአርትኦት ሥራ እንዲሰሩለት አድርጓል። አርትኦቱን ስላላጉላሉበትም ደስተኛ ነው። በአንድ ወር ውስጥ አጠናቀው ነው የመለሱለት። ከዚህም በላይ የጠራ ሥራ ለማውጣት ሲል ለሌሎችም ጓደኞቹ ዳግመኛ ሰጥቷል። ከዚያ መፅሃፍን ለማሳተም የሚያስፈልጉ ግባአቶችን ወሰደ።

ዶክተር ሐብታሙ የአርትኦት ሥራው በዚህ ብቻ እንዲቆም አልፈለገም። የመጨረሻ መፅሃፉን በአማርኛም ሆነ በኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች እጅ እንደሚያስገባው ስለሚያውቅ ያለምንም እንከን እንዲወጣለት በኦሮምኛ ቋንቋ ዲግሪ ወይም ማስተር ያለው ተማሪ መፈለግ ጀመረ። ነገር ግን በዚህ ዘርፍ የተማረ ሰው ለማግኘት ቀላል አልሆነለትም። በብዙ ልፋት ነው የኦሮሚኛ ቋንቋ አስተማሪና ፅሁፎችን አርትኦት የሚያደርግ ሰው ያገኘው። ለአንድ ወር ያህል የአርትኦት ሥራው ፈጅቷልም። ከዚያ የመጨረሻ እርማቶችን ከአደረገ በኋላ መፅሃፉን ለህትመት አበቃ።

እርሱ ቋንቋውን በሚማርበት ጊዜ ለመጀመሪያ ጊዜ ያገኛቸው መፅሃፎች ወይ መዝገበ ቃላት አልያም ደግሞ ንግግር ነበሩ። ይህም የኦሮሚኛ ቋንቋ ለማያውቅና መማር ለሚፈልግ ሰው በቂ አይደለም። የኦሮሚኛ ቋንቋ ሕግ ለማወቅ ለሚፈልግ ሰው የተፃፈ መፅሃፍ የለም። በኦሮሚኛ ቋንቋ ላይ የተፃፉ የሰዋሰው መፅሃፎች ቢኖሩም የተዘጋጁት በኦሮሚኛ ቋንቋ በመሆናቸው መረዳት አይቻልም።

ሰዎች ራሳቸው በሚያውቁት ቋንቋ ቃላትን፣ አረፍተ ነገሮችንና አገላለፆችን ሊያውቁ ይገባል። የሚያውቋቸውን ቋንቋዎች ለመጠቀም ደግሞ የቋንቋውን ሕግ ማወቅ ግድ ነው። ዝም ብሎ ቃል ማወቅ ብቻ ጥቅም የለውም። ለዚህም ነው ዶክተር ሐብታሙ በአማርኛ ቋንቋ የተፃፈ የኦሮሚኛ ቋንቋ ሰዋሰው መፅሃፍ ያዘጋጀው።

ለመዝገበ ቃላትና ለንግግር በአማርኛ፣ በእንግሊዘኛና በኦሮሚኛ ቋንቋዎች እንደተዘጋጁት መፅሃፎች የኦሮምኛ ቋንቋ ሰዋሰው በሁለትና ሦስት ቋንቋዎች አልተዘጋጀም። ሕጉን ካወቀ በኋላ በኦሮሚኛ ብቻ የተፃፉትን የሰዋሰው መፅሃፍት ወደ ማንበብ ይሸጋገራል። ይህንኑ ክፍተት በመረዳት መፅሀፉ ቢታተም ክፍተቱን ይሞላል በሚል ‹‹ሪቂቻ›› ወይም ድልድይ ሲል ዶክተር ሐብታሙ መፅሃፉን ሰይሞ ለንባብ አብቅቶታል። መፅሃፉም ሰዎች በአማርኛና በኦሮሚኛ ቋንቋ መሰረታዊ ሰዋሰው እንዲረዱ የሚያስችል ነው።

‹‹ቋንቋ መግባቢያም ክህሎትም ነው›› የሚለው ዶክተር ሐብታሙ፤ ቋንቋን በቀላሉ መማር እንደሚቻልና ሰዎች ቋንቋን በአወቁ ቁጥር የመግባባት ችሎታቸውን ይበልጥ ለማሳደግ እድል እንደሚያገኙ ይናገራል። ማንም ሰው ተጨማሪ ቋንቋ ቢያውቅ የማይጠላ በመሆኑ ፍላጎት እንዳለ ሆኖ ይህን ፍላጎት እውን ለማድረግ ግን የራስ ጥረት እንደሚያስፈልግ ያስረዳል።

ሰዎች አፋቸውን ከፈቱበትና ከሚያውቁት ቋንቋ በተጨማሪ በሚኖሩበት ማህረበረሰብ ውስጥ ያሉ ቋንቋዎችን ቢማሩ ሊቀላቸው እንደሚችሉም ነው ዶክተር ሀብታሙ የሚናገረው። ከዚህ አንፃር በርካታ አጋጣሚዎች ስለሚኖሩ የአገር ውስጥ ቋንቋዎችን በአጠረ ጊዜ በቀላሉ መማር እንደሚችሉ ይመክራል። ዋናው ጉዳይ ግን በውስጥ ያለ ፍላጎት መሆኑንም ይጠቅሳል።

ቋንቋዎች መደባቸው የሚለያይ ቢሆንም በማህረሰቡ ውስጥ ግን ይወራረሳሉና በቀላሉ ለመልመድ አያስቸግሩም። በዚያ ላይ ቋንቋ የአንድን ማህበረሰብ አስተሳሰብና ባህል የሚገልፅ በመሆኑ ሰዎች ከሚያውቋቸው ቋንቋዎች በተጨማሪ ሌሎችንም ቋንቋዎች የማወቅ እድል እንዳላቸው ያነሳል። ለዚህም እርሱ ጥሩ ምሳሌ እንደሆነ፤ ከዚህ በፊት ለታካሚዎቹ አገልግሎት ሲሰጥ አስተርጓሚ ይጠቀም እንደነበርና ቋንቋውን በማወቁ አሁን ላይ በቋንቋው መግባባት እንደቻለ ያስረዳል።

ዶክተር ሐብታሙ ወጣቶች በፍላጎት ብቻ ሳይሆን የመከባበር፣ የመቻቻልና የመዋደድ እሴቶችን እንዲያዳብሩ የሁሉንም ብሄረሰቦች ቋንቋ መማር አለባቸው ይላል። ይህም ይጠቅማቸዋል እንጂ አይጎዳቸውም። ቋንቋ ክህሎትና መግባቢያ እንዲሁም እውቀትን መገንቢያ እንደሆነ አውቆ መጠቀም ያስፈልጋል። የኦሮምኛ ቋንቋን አብዛኛው ማህበረሰብ የሚጠቀምበት እንደመሆኑ ሌሎች ፍላጎቱ ያላቸው ሰዎች ቋንቋውን የራሳቸው አድርገው ቢማሩ ለቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ ያላቸውን አክብሮት ማሳያም ነውና ብንገለገልበት መልካም ነው ይላል።

እያንዳንዱ ሰው ቋንቋ የሚማረው ለራሱ እንጂ ለሌላ ሰው ብሎ አይደለም። ስለሆነም ለቋንቋ ያለው አረዳድ በሰፋ መልኩ መሆን ይኖርበታል። ሰዎች ሁሉንም ቋንቋ የኔ ናቸው ሲሉ የሚያገኙት ነገር ይበዛላቸዋል። ስለዚህም ለመብዛት፣ ለማወቅና ከፈለግነው ሰው ጋር በመግባባት ለመኖር ከፈለግን ቋንቋን እንማር ይላል።

‹‹ሪቂቻ›› የተሰኘው የኦሮሚኛ ሰዋሰው ቋንቋ ከታተመ አምስት ወራት ሆኖታል። ለህትመት ከበቃ ወዲህ ከአንባቢያን የሚመጡ ግብረ መልሶችም ገምቢ ናቸው። መፅሃፉ እንዲታተም በማህበራዊ ድረገፅ እንዲወጣ ተደርጓል። ይህንኑ ተከትሎ አንዳንድ ሰዎች መፅሃፉን ለማስተዋወቅ እገዛ አድርገዋል።

በመጀመሪያ አንድ ሺህ ቅጂ የታተመ ሲሆን፤ በዚህ ቁጥር በርካታ ሰዎች ጋር መድረስ የማይቻል በመሆኑ መፅሃፉ በማህበራዊ ድረገፅ በተለይ ደግሞ በፌስቡክና በቴሌግራም ቻናል እንዲተዋወቅ ተደርጓል። በዚህም በርካታ ተደራሲያን ጋር መድረስ ተችሏል። ተደራሲያንም የተለያዩ ገንቢ አስተያየቶችን እየሰጡ ይገኛሉ። ስለዚህም በግምገማዬ መፅሃፉ ጥሩ ተቀባይነትን አግኝቷል።

ጀርባ ታሪኬ ሲታይ እኔ የኦሮሚኛ ቋንቋ ተናጋሪ አይደለሁም። መፅሃፉንም ያዘጋጀሁት ክፍተቶቼን አይቼ ነው። በዚሁ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱና ከኔ በተሻለ ሊፅፉ የሚችሉ ሰዎች ይኖራሉ። ነገር ግን እስካሁን ትኩረት የተደረገው የኦሮሚኛ ቋንቋን ለሚያውቁት ብቻ ነው። ቋንቋውን ለማያውቀው ማህበረሰብ የሚደረገው ጥረት እንዳለ ሆኖ ሌሎችም ቢማሩበት ማለት ያስፈልጋል። ለዚህም የእርሱ መጸሐፍ ማሳያ ይሆናል።

በቀጣይም የኦሮሚኛ ቋንቋ ተናጋሪ ህመምተኞች እንዴት የህክምና እንክብካቤ ማግኘት ይችላሉ የሚሉ መፅሐፍትን ይዞ ብቅ እንደሚል ቃል የገባው ዶክተር ሐብታሙ፤ ለዚህም መነሻው በዘርፉ የተጻፉ መጻሐፍትን ማግኘት አለመቻሉ ነው። እናም በተለይ ታካሚዎች ከሀኪሞች ጋር ሲገናኙ በቋንቋ እንዳይቸገሩ ሊያግዝ የሚችል መፅሃፍት ለማዘጋጀት እቅድ አለው። ችሎታውን እያየና ቋንቋውን እየተማረ ሌሎችንም ሥራዎችን ይዞ ብቅ ማለቱ እንደማይቀር ያነሳል።

# በከበሩ ማዕድናት ዙሪያ ያሉት ተስፋዎች



ስምስም መንግሥቱ

ድንጋይ ይመስላል፤ የተፈለጠ ድንጋይ፤ በውስጡ ከፍተኛ ገንዘብ የሚያስገኝ ውድ ሀብት የያዘ ነው ብሎ ለመገመት ጥቂትም ቢሆን ስለከበሩ ማዕድናት ግንዛቤ ያለው ሆኖ መገኘትን ይጠይቃል።

ከላይ የሚታየው የማእድኑ ነጩ ክፍል ቶሎ እይታ ውስጥ ይገባል፤ ዋናው፣ አብረቅራቂው፣ ደማቅ የወይን ጠጅ ቀለም ያለው ቀልብን በእጅጉ የሚስበው የማእድኑ ክፍል ግን ከውስጥ ነው ያለው። ይህ አብረቅራቂ የከበረ ማዕድን እሴት ተጨምሮበት ለቀለበትና ለአንገት ጌጣጌጥ ፈርጥ አገልግሎት እንዲውል ተደርጎ ለገበያ ተዘጋጅቶም እዚያው ተመለከትኩ።

ይህንና ሌሎችንም የከበሩ ማዕድናትን በጥሬውና እሴት ጨምረው ለውጭ ገበያ በማቅረብ በላኪነት ሥራ ላይ የተሰማሩት አቶ መሐመድ ነዚብ አብረቅራቂው የወይን ጠጅ ቀለም ያለው ይህ የማእድን አይነት አመቲስት እንደሚባልና በኦሮሚያ ክልል ጉጂ ዞን ሻኪሶ እንደሚገኝ ይገልጻሉ። የሻኪሶ ምድር ጋርኔት የሚባል ማእድን መገኛም ነው።

በአካባቢው ስም የተሰየመውን የወሎ ኦፓልና ኤመራልድ የተባለውን ማዕድንም አቶ መሐመድ በጥሬውና እሴት በመጨመር ለውጭ ገበያ ያቀርባሉ። አማራ ክልል ደላንታ አካባቢ የሚገኘው ኦፓል በሌላው የዓለም ክፍልም ይታወቃል።

አቶ መሐመድ ኢትዮጵያ በምድር ውስጥ በርካታ በረከቶች እንዳሏት የበለጠ ግንዛቤ ያገኙት የማእድን ሀብቱን በመላክ ሥራ ላይ ከ15 ዓመታት በላይ በቆዩባቸው ጊዜያቶች እንደሆነ ይገልጻሉ። «የማዕድን ሀብቱ ሻኪሶ ቦረና በሌሎችም የአገሪቱ ክፍሎች በስፋት ይገኛል። በማህበረሰቡ ውስጥ በቂ ግንዛቤ ባለመኖሩ ጥቅም ላይ ውሎ ከፍተኛ ገቢ የሚያስገኝ የማዕድን ሀብት እንደዋዛ እየታየ ነው። እየረገጥነው፤ እየሄድንበት ነው ሲሉም በቁጭት ይናገራሉ።

ልማቱ የሚከናወነው ስለማዕድን ሀብት ሰፋ ያለ ግንዛቤና እውቀቱ ባላቸው እንዳልሆነና በዘመናዊ መሳሪያ ወይንም ቴክኖሎጂ አለመታገዙን ጠቅሰው፣ በዚህ የተነሳም አልሚውም ሆነ በውጭ ገበያ ላይ የተሰማራው በሚፈለገው ልክ ተጠቅሞ ራሱንም ሆነ የአገር ኢኮኖሚን በሚያሳድግ መልኩ ውጤት እንዳላስገኘ ያስረዳሉ።

በቅርቡ በአዲስ አበባ ከተማ በተካሄደው የማዕድን ቴክኖሎጂ ኤክስፖ ላይ ያዩዋቸው አገር በቀል የወርቅ ማጠቢያና እና ሌሎችም ማሽኖች ለልማቱ ተስፋ የሚሰጡ ሆነው እንዳገኙዋቸውም ተናግረው፣ ወደፊት በዘርፉ ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገብ እንደሚቻልም ይናገራሉ።

አቶ መሐመድ በአልሚውና በላኪው መካከል የሚደረገው ግብይትም በድርድር እንደሚፈጸም ገልጸዋል። እስካሁን ባላቸው ተሞክሮም ይህን አይነቱን ግብይት የሚያካሂዱት በአገር ውስጥ ብቻ ሳይሆን፣ ከህንድ ከሚመጡ ደንበኞቻቸው ጋርም ነው። ወደፊት ወደተለያዩ የዓለም አገራት ገበያ በማፈላለግ ምርቱን ለማቅረብ የተዘጋጁትም በዚሁ የድርድር ሥርአት ነው።

ነፃ የገበያ ሥርአት የተከተለው ግብይት ምርቶችን በውድ ዋጋ በመሸጥ የተሻለ ገቢን በማስገኘት ጥቅሙ የጎላ መሆኑን አቶ መሀመድ ይገልጻሉ። የኢትዮጵያ የማዕድን ሀብት በሌላው ዓለም ተፈላጊ መሆኑን ጠቅሰው፣ የመነሻ ዋጋ ሳይኖረው በድርድር ለውጭ ገበያ ማቅረቡ ግን ጉዳቱ እንደሚያመዝን ነው ያስገነዘቡት።

በአገር ደረጃ የመነሻ መሸጫ ዋጋ እንደሚያስፈልግ ለውጭ ገበያ በማቅረብ በሥራው በቆዩ በአንዳንድ የከበሩ ማዕድናትና ጌጣጌጥ ላኪዎች በቅሬታ ይነሳ እንደነበር ይታወሳል። በዚሁ ጉዳይ ላይ ከወራት በፊት ከማዕድን ሚኒስቴር ጋር መድረክ ከነበራቸው ላኪዎች ጋር በተደረገ ውይይት የከበሩ ማዕድናትና ጌጣጌጥ በአገር ደረጃ የመሸጫ መነሻ ዋጋ መውጣት እንዳለበት ስምምነት ላይ መደረሱም ይታወቃል።

በላኪነት ዘርፍ ላይ የተሰማሩት ሌላው ያነጋገርናቸው ቡምሪንግ የተባለ የማዕድንና ጌጣጌጥ ላኪ ኩባንያ ባለቤት አቶ መከተ ላቀው በአውስትራሊያ ዳይመንድ የተባለውን የማዕድን አይነት ለጌጣጌጥ በማዋል ሰፊ ተሞክሮ ባለው ኩባንያ ውስጥ ሰርተዋል፤ በዘርፉም ተሞክሮ ማካበት ችለዋል።

ወደ አገራቸው መጥተው ዘርፉን ከተቀላቀሉም ሁለት ዓመታት ሆኗቸዋል። ዘርፉን ሊያግዝ የሚችል የቴክኖሎጂ ትምህርትም እንዳላቸው የሚናገሩት አቶ መከተ፣ ልምድና ክህሎታቸውን ብቻ አይደለም ይዘው ወደ አገር ቤት የመጡት። በአውስትራሊያ ይሰሩበት በነበረው ኩባንያ ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውለውን ከመሬት ውስጥ ተቆፍሮ የወጣውን ማዕድን ፖሊሽ ወይንም ማዕድኑን ብቻ ጥርት አድርጎ በቅርጽ የሚያወጣና ለመቁረጫ አገልግሎት የሚውሉና ሌሎችንም ለማዕድን ሥራ የሚያገለግሉ መለስተኛ መሣሪያዎች ይዘው በመምጣት ነው ኩባንያቸውን ያቋቋሙት።

ወደ አገራቸው ይዘው የመጡትን ተሞክሮ፣ ክህሎትና ቴክኖሎጂ ለራሳቸው ብቻ አልተጠቀሙም፤ በተመሳሳይ የሥራ ዘርፍ ላይ ለሚገኙ በማካፈል ጭምር ዘርፉ በጋራ እንዲያድግ ጥረት በማድረግ ላይ መሆናቸውን ይገልጻሉ። በተለይም ተሞክሮን የማካፈል ፍላጎት እንዳላቸውና ብዙ ጊዜያቸውንም ለእዚህ አላማ እንደሚያውሉ ይናገራሉ።

በነዚህ ዓመታትም አጌት፣ የወሎ ኦፓል፣ አጃራ፣ ኦብሲዲያ ኤመራልድ ሩቢ ሳፋየርና ሌሎችም ለጌጣጌጥ የሚውሉ ማዕድናትን ለጌጣጌጥ በሚውል መልኩ በማዘጋጀት ወይም ፖሊሽ በማድረግና እሴት የተጨመረበት ጌጣጌጥ ለውጭ ገበያ ሲያቀርቡ ቆይተዋል።

እርሳቸው እንዳሉት፤ በአውስትራሊያ የማዕድን ልማትና እሴት የተጨመረበት ምርት ለገበያ ለማቅረብ ያለው ሂደት ኢትዮጵያ ውስጥ ካለው አሰራር ጋር ፍጹም ይለያል። በአውስትራሊያ አልሚው በልማቱ ሥራ ላይ እንዳይጎዳ ከሚደረገው የጉዳት መከላከያ ጥንቃቄ ጀምሮ ልማቱ በቴክኖሎጂ ታግዞ ነው የሚከናወነው። በአልሚው በቁፋሮ የተገኘው ማዕድንም ፖሊሽ የሚሆነው በዘመናዊ መሳሪያ በመታገዝ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ልማት ከባህላዊ አሰራር የተላቀቀ እንዳልሆነ ነው በአጭር የሥራ ቆይታቸው የታዘቡት።

ዘርፉ በዘመናዊ አሰራርና በዘርፉ ባለሙያዎች እንዲከናወን ማድረግ አሁንም አልረፈደበትም የሚሉት አቶ መከተ፣ እርሳቸውም በሥራና በትምህርት በውጭ አገር ያገኙትን ተሞክሮ ይዘው ወደ አገር ቤት በመምጣት በሥራው ሲሰማሩ ለውጥ ለማምጣት ከራሳቸው ለመጀመር በማሰብ እንደሆነ ነው ያጫወቱን።

የማእድን አልሚው ደህንነት መጠበቅ እንዳለበትም አጽንኦት ሰጥተው ይናገራሉ። የአልሚው ደህንነት ካልተጠበቀ ዘርፉ በከፍተኛ ደረጃ ለአገር ኢኮኖሚ እድገት ያስገኛል ተብሎ የሚጠበቀውን ገቢ ለማግኘት እንደሚያስቸግር ነው የገለጹት።

እርሳቸው እንዳሉት፤ በማዕድን ፍለጋ ወቅት በሚከናወነው የቁፋሮ ሥራ በሚያጋጥም የተራራ ናዳ እና በሌሎችም ከሥራ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች አልሚው ለጉዳት ሊዳረግ ይችላል። በዚህ ረገድ መንግሥት ልማቱ በሚከናወንበት አካባቢ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ በመሥራት ንቃተ ህሊናን ከፍ ማድረግ ይጠበቅበታል። ይህ ካልሆነ ገንዘቡን ይዞ ወደ ልምቱ የሚገባው ባለሀብትም ቢሆን ለደህንነት ትኩረት አይሰጥም። በነበረው ነው የሚቀጥለው።

የማዕድን ልማቱም በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ካልታገዘ ማዕድኑ ይሰባበራል። ይህ ደግሞ የጥራት መጓደል ያስከትላል። ማዕድኑ በቁፋሮ ሲሰባበር መጠኑ ያነሰ ምርት ነው የሚገኘው። በዚህ ወቅት መንግሥት ለዘርፉ የሰጠው ትኩረት እነዚህን ሁሉ ክፍተቶች የሚቀርፍ እንደሚሆን ተስፋ አድርገዋል።

አቶ መከተ ኩባንያ በማቋቋም ወደ ሥራው የገቡበት ወቅት በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል በነበረው ጦርነት እንዲሁም በዓለም ላይ በተከሰተው ኮቪድ 19 ቫይረስ ወረርሽኝ ምክንያቶች የዘርፉ እንቅስቃሴ የተቀዛቀዘበት ነበር፤ አገር ችግር ውስጥ በምትወድቅበት ጊዜም ቢሆን ባለሀብቱ መስራት እንዳለበት አስገንዝበው፣ ስራው በመንግሥት ላይ ብቻ የሚጣል መሆን እንደሌለበት ነው የገለጹት። በችግሩ ወቅትም ኩባንያቸው ሥራውን አንዳላቋረጠ ተናግረዋል። በአጠቃላይ ዘርፉ የበለጠ ውጤታማ መሆን የሚችለው አገር ውስጥ ሰላምና መረጋጋት ሲኖር እንደሆነ አመልክተዋል።

ማዕድን ሚኒስቴር ኤክስፖ በማዘጋጀት አልሚውንና ላኪውን እንዲሁም ቴክኖሎጂ አቅራቢውን በማገናኘት ዘርፉን ለማነቃቃት እያደረገ ያለው እንቅስቃሴም በዘርፉ የተሰማራው የበለጠ እንዲሰራ፣ የውጭና የአገር ውስጥ አዳዲስ ኢንቨስትመንት ለመሳብ የሚያግዝ ሆኖ እንዳገኙት የሚናገሩት አቶ መከተ፣ ደማቅ ብለው በገለጹት የማዕድንና ቴክኖሎጂ ኤክስፖ ላይ መሳተፋቸው እንዳስደሰታቸውም አስታውቀዋል።

ኤክስፖው ከገበያ ትስስር ባለፈም በዘርፉ የተሰማራውን እርስበርስ በማስተዋወቅ ጥሩ ተሞክሮ የተገኘበት ሆኖ ነው ያገኙት። ኤክስፖው በዓመት ሁለቴና ሶስት ጊዜ ቢካሄድ የውጭ ገበያንና ኢንቨስትመንት ለመሳብ ጠቃሚ እንደሚሆን ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያ በማእድን ዘርፍ በኢኮኖሚ የሚያጋጥማትን የውጭ ጫና ለመቋቋም የሚያስችል በቂ ሀብት አላት የሚሉት ሌላው አስተያየት ሰጪ አቶ ባህሩ ይርጋ ናቸው።በአገሪቱ አልምቶ ወደ ጥቅም የሚቀይራቸው እጆችን የሚጠብቁ የማዕድን ሀብቶች እያሉ በእርስ በርስ ግጭት የልማት ጊዜ መባከኑን በቁጭት ይገልጻሉ።

በትግራይ ክልል እጅግ ውድ ዋጋ የሚያወጣ ሳፋየር የተባለ ማዕድን መኖሩን በመጠቆም፣ በአካባቢው ላለፉት ዓመታት በተካሄዱት ጦርነቶች ሳቢያ የማእድን ሀብቱ ጥቅም ሳይሰጥ መቆየቱን ይገልጻሉ። ማዕድን የሀብት ምንጭ እንደሆነ ግንዛቤ የተያዘውና በመንግሥት ትኩረት የተሰጠው በቅርብ ጊዜ አንደሆነም ነው የገለጹት።

ኤመራልድ፣ ሞርጋናይት፣ ሩፒ፣ ቶፓዝና ሌሎችንም የማዕድን አይነቶች ከሻኪሶ፣ቦረናና ከሌሎችም የአገሪቱ ክፍሎች በመግዛት ለውጭ ገበያ እያቀረቡ መሆናቸውን ጠቅሰው፣ ዘርፉ ለብዙ ዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠር ኢኮኖሚያዊ ፋይዳው ከፍተኛ እንደሆነም ይናገራሉ።

በቅርቡ በኢትዮጵያ በተካሄደው የማዕድንና ቴክኖሎጂ ኤክስፖ ላይ ተገኝተው ንግግር ያደረጉት የኢፌዲሪ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ እንዳሉት፤ ኢትዮጵያ ውስጥ የማዕድን ሀብት ለኢኮኖሚው እያበረከተ ያለው አስተዋጽኦ ዝቅተኛ ነው፤ ልማቱ ላይ በመሥራት ለውጥ ማምጣት ያስፈልጋል።

«ኢትዮጵያ በውስጧ የያዘችውን ሚስጥር ገና አናውቀውም» ሲሉም ጠቅሰው፣ ተመራማሪዎች ጠንክረው ከሰሩ ለግብርናው፣ ለኢንዱስትሪው፣ ለግንባታው ለሌሎችም የኢኮኖሚ ዘርፎች ግብአት የሚውል እምቅ የማእድን ሀብት አገሪቱ እንዳላት አስታውቀዋል። ይህን በማልማት በግዥ ከውጭ የሚገባውን የማእድን ምርት መተካት እንደሚቻል በተለያየ ጊዜ ከሚሰጡ መረጃዎች መገንዘብ ይቻላል ብለዋል።

ፕሬዚደንቷ የማዕድን ሀብት አላቂ እንደሆነ ግንዛቤ መያዝ እንዳለበት ጠቁመው፣ የማእድን ሀብቱን በአግባቡ መጠቀም እንደሚገባ አስገንዝበዋል። ኢትዮጵያ ገና ያልተነካ ሀብት እንዳላትና ለማልማት የሌሎች አገሮች ተሞክሮ ትምህርት ሊሆን እንደሚችልም ጠቁመዋል።

«የማዕድንና ቴክኖሎጂ ኤክስፖ የማእድን ሀብቱ ባለቤት የሆነው ኢትዮጵያዊ ሀብቱን ጠንቅቆ እንዲያውቀው ብቻ ሳይሆን፣ ተንከባክቦና ጠብቆ ጥቅም ላይ የሚውልበትንና ከዘርፉም ተጠቃሚ የሚሆንበትን ሁኔታ እንዲያመቻች ያግዛል» ሲሉም ፕሬዚደንቷ መናገራቸው ይታወሳል።

ፕሬዚደንቷ ኢትዮጵያ የበርካታ የማዕድን ሀብቶች ባለቤት እንደሆነች የማያውቁ አገራት መኖራቸውንም የአፍሪካ ልማት ባንክ ባዘጋጀው የአፍሪካ ኢንቨስትመንት ፎረም ላይ መጥቀሳቸውን አስታውሰው፣ አንዳንድ የመድረኩ ተሳታፊዎች ያነሳቸው ከነበሩ ጥያቄዎች ከኢትዮጵያ ውጪም የኢትዮጵያን የማእድን ሀብት የማወቅ ጉጉት መፈጠሩን መገንዘብ መቻላቸውን ጠቅሰዋል።

ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው ሌላው ዓለም የኢትዮጵያን የማእድን ሀብት በተገቢው ሁኔታ እንዲያውቀው አለመደረጉን እንደሆነም አመልክተዋል። በዚህ ረገድም ብዙ ሥራ እንደሚቀር ያሳያል ብለዋል።

ውስጣዊ ችግሮች እየተፈቱ እንደሆነና በዘርፉ የሚሰማሩ ኢንቨስተሮች እንደሚመጡ ተስፋ ያደረጉት ፕሬዚዳንቷ፣ በዘርፉ የሚስተዋለውን ህገወጥነት በመከላከልና ህጋዊ መስመር በማስያዝ ረገድም ሥራዎች መሰራት እንዳለባቸው አሳስበዋል። መንግሥት ለዘርፉ የተለያዩ ድጋፎችን በመስጠት እያደረገ ያለውን እንቅስቃሴም አበረታች መሆኑን ተናግረዋል።

መንግስት የዘርፉን እምቅ ሀብት እና ሀብቱን ለማልማት በሚደረገው ሂደት የሚያጋጥሙ ችግሮችን በሚገባ እየተገነዘበ፣ መፍትሄያቸውንም እያመላከተ ይገኛል። በአገር በቀል ኢከኖሚ ሪፎርሙ የአስር አመት መሪ እቅድ የማእድን ዘርፉን ከአምስቱ የምጣኔ ሀብቱ ምሰሶዎች አንዱ ማድረጉንም ከዚሁ አኳያ መመልከት ይቻላል።

ከላኪዎቹ መገንዘብ እንደቻልነው ለአንዳንድ አገራት የእድገት ምንጭ የሆነው የማዕድን ሀብት በኢትዮጵያም ቢገኝም፣ አህገሪቱ ይህን እምቅ ሀብት በተገቢው መንገድ ባለማልማቷና እሴት የተጨመረበት አገልግሎት ለገበያ አቅርባ መጠቀም ባለመቻሏ እሳቸው ቁጭት አድሮባቸዋል።

በአልሚዎቹ፣ በላኪዎችና በመንግሥት በኩል በአብዛኛው እየተከናወነ ያለው ተግባር እሴት ያልተጨመረበት ጥሬ እቃ በመላክ ላይ የተመሰረተ ነው። ይህም አገርን ሳይሆን ሌሎች አገሮችን ነው የበለጠ ተጠቃሚ የሚያደርገው፤ ይህ ሁኔታ መቀየር ይኖርበታል። ቁጭት አንድ ነገር ነው፤ ብቻውን ግን ፋይዳ የለውም፤ ማእድኑን ለማልማት በሁሉም ወገን የተፈጠረው ተነሳሽነት ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## ጥቁር አምልኮ

በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)

አያቴ ጥቁር ቀለም አትወድም..ጠይም መሆኔ በጀኝ እንጂ እኔንም ልጇ አይደለም ብላ ልትክደኝ ትሞክር ነበር። ከቤታችን ውስጥ ለጥቁር የቀረብኩት ጠይሙ እኔ ነኝ..አብሬያት ስሆን ሌላ ወሬ የላትም ‹እንዳው በማን ወጥተህ ነው እንዲህ የጀበና ቂጥ የመሰልከው? በዘራችን እንዳንተም የለ! ትለኛለች። አይኗን፣ ቀልቧን ፊቴ ላይ በጥርጣሬ ጥላ ማንም ባላስተዋለኝ አይነት እያስተዋለችኝ። አያቴ የእርጅናዋን ግማሹን ያሳለፈችው በእኔ መልከ ልውጥነት ስትፈላሰፍ ነው። የልጅ ልጇ መሆኔን አምና ለመቀበል ብዙ ጊዜ ፈጅቶባታል። ይሄን ሁሉ ዘመን አብሬያት እየኖርኩ እንኳን ከሌላ የተወለድኩ እንጂ ከእሷ ዘር የመጣሁ አይመስላትም። አሁንም እንኳን ሳታምነኝ አብሬያት የሆንኩ ያህል ነው የሚሰማኝ።

አያቴ ለምን ጥቁር ሰው እንደምትጠላ ለማወቅ ብዙ ለፍቼ አልተሳካልኝም። ከሁሉም የከበደኝ ግን ጥቁር መልክ ያላትን፣ በጣም የማፈቅራትን ፍቅረኛዬን አያቴ ፊት ማቅረብና ፍቅረኛዬ ናት ተዋወቂያት ማለት ነበር። የእኔ ጠይምነት ኩርፊያ ሆኗት ጠዋትና ማታ ለምትነጫነጨው አያቴ፣ በመልኬ ብቻ የልጅ ልጇ አይደለም ብላ ልትክደኝ ላመል ለቀራት ሴት፣ የእኔን ጠይምነት አምና ሳትቀበል ሌላ ጥቁር ሴት ይገባት ብሄድ የምትሆነውን መሆን ሳስበው ፈራሁኝ። ምን አለፋችሁ ፍቅረኛዬን ለአያቴ ለማስተዋወቅ የተቸገርኩትን መቸገር አጠይቁኝ። ጥቁሯን ፍቅረኛዬን ትዝታን ጎኔ አስቀምጬ በግራ መጋባት ተቀምጫለው..ጠረጴዛውን በጣቴ እየጠበጠብኩ።

ከትዝታ ጋር ሳንጣላ የዋልንበት ቀን የለም.. የመጣላታችን ዋናው ምክንያት ደግሞ አያቴ ናት። እሷ መቼ ነው ቆይ አያትህን የምታስተዋውቀኝ? ትለኛለች።

‹ዛሬ ትንሽ አመም ስላደረጋት ሲሻላት የዛሬ ሳምንት አስተዋውቅሻለው እላታለው። መልሷ ሁሌም እሺ ነው። እኔ ብያት እንቢ ብላኝና ተቃውማኝ አታውቅም። አያቴን ታማ አታውቅም..ትዝታ ፊት በግድ የማሳምማት እኔ ነኝ። በንግግሬ ውስጥ ውስጡን ፍርሃት ይይዘኛል.. የዛሬ ሳምንት ሲሻልሽ አስተዋውቅሻለው ማለቴ ያስቃል.. የዛሬ ሳምንት እንደሚሻላት በምን አወክ ብትለኝ እኮ የምመልስላት የለኝም። ከነውሸቴ..ከነነውሬ ትዝታ ዝም ትለኛለች። የዛሬ ሳምንት ይረድስና ‹ዛሬ እኮ አያትህን የምታስተዋውቀኝ ቀን ነው..ረሳኸው እንዴ? ትለኛለች ተንዘላዝዬ ምንም ዝግጁነትን ስታጣብኝ።

‹ባክሽ አልተሻላትም..! ብዬ እዋሻታለው። ራሴ በፈጠርኩት የአያቴ ህመም ፊቴን የሀዘን ጥላ አልብሼ። ብዙ ሳምንታት አለፉ..አያቴ አልዳነችም። ከዚህ በኋላ ትዝታ ‹አያትህን መጠየቅ ያለብኝ ሲድኑ ሳይሆን ታመው እያለ ነው..ደሞ ሚስትክ አይደለሁ! ላስታምማቸው ይገባል› ስትለኝ ልዋሽ የማልችልበትን ወሬ ነገረችኝ። የአያቴን የጥቁርነት ጠል ስለማውቀው..ሌላ ሰበብ ፈጥሬ አይሆንም ማለት ነበረብኝ። ግን እንቢታዬ ትዝታን አላራራትም አስቆጣት እንጂ። ለአንድ አመት በዚህ ሁኔታ ውስጥ ነው ያለፍነው። ዛሬም አያቴን አስተዋውቅሻለው ብያት እንደዚህ ቀደሙ ለብሳና ተውባ መጥታ ሳንገራግርባት ተኳርፈን ተቀምጠናል።

ስንገናኝ ጥቂት የፍቅር ቃላትን መለዋወጥ ግድ ነው.. ከንፈሬን ወይ ጉንጬን ብቻ ለከንፈሯ የቀረባትን አንዱን ነገሬን ስማ..ክንዷን ትከሻዬ ላይ ጣል አድርጋ ጎኔ አረፍ ትላለች። ትዝታ ሳትደገፈኝ ተቀምጣ አታውቅም። ስትቀመጥ እሷ ስንራመድ እኔ እንደተደገፍኳት ነው። ለትንሽ ጊዜ ፍቅራችን ያስቀና ነበር..አያቴ እስክትነሳ ድረስ። ከአያቴ በኋላ ሌላ ነን። ‹ቆይ መቼ ነው ከአያትህ ጋር የምታስተዋውቀኝ? ትለኛለች ተደግፋኝ..ወድቃብኝ.. አይኔን እያየች። በነገራችሁ ላይ አይኔን ሳታይ አውርታኝ አታውቅም። ወሬዋ አስጨናቂ ሆኖብኝ ፊቴን ሳዞርባት እንኳን በእጇ አገጬን እየመለሰች አይን አይኔን እያየችኝ ነው የምታወራኝ። ለፍቅር ማን እንደ ትዝታ?

የምላት ጠፍቶኝ ዝም እላለው..ፊቴን ወደ ሌላ አቅጣጫ እያዞርኩ።

‹አትሰማም? ከአያትህ ጋር መች ነው የምታስተዋውቀኝ? ስትል ትደግምልኛለች..ወደ ሌላ የዞረ ፊቴን አገጬን በመጠምዘዝ እያስተካከለች። ሊቀየምና ሊያኮርፍ ላመል በቀረው ፊት። ከዚህ ጥያቄ በኋላ እኔና ትዝታ የሁለት ዓለም ሰዎች ነን..ተስማምተን አናውቅም። ፍቅራችን ማቅ የሚለብሰው ይሄን ጥያቄ ተከትሎ ነው። ምን መመለስ እንዳለብኝ ጠፍቶኝ ዝም እላለው።

‹ቆይ አንተ እየቀለድክብኝ ነው እንዴ? ቤተሰብ ከሌለህ ወይ የለኝም በለኝ› ትለኛለች።

‹እንደዛ አይደለም እኮ ፍቅር› እላለው ተለሳልሼ ስለ አያቴ ለመናገር ድፍረት በማጣት።

‹ታዲያ ምንድ ነው? አስተዋውቅሻለው እያልከኝ ሁለት ዓመት ሞላን›

መልስ አጥቼ ጠረጴዛውን እጠበጥባለው..ጠረጴዛውን መጠብጠቤ ያበግናታል መሰለኝ ትሸፍትብኛለች።

‹ዛሬ ካላስተዋወከኝ እመአምላክን..

በተቀመጥኩበት ውሀ ሆንኩ። ልቤ በአፌ ልትሾልክ ቃተትኩ። ትዝታ ከማለች ቀልድ አታውቅም..በተለይ በእናቷ..በተለይ በእማአምላክ..። እማምላክን ብላ ውሸት ሆና አታውቅም..መህላዋ ለዘላለም ሊያቆራርጠን እንደሚችል ሳስብ አየር አጠረኝ። ጉሮሮዬ ለትንፋሼ ጠበበው..። ደግነቱ እመአምላክን ብላ አልቀጠለችም..ዝም ነው ያለችው። ዝምታዋ ግን ረፍት ነሳኝ..እመአምላክን ብላ ዝም ከምትል ያሰበችውን ብትነግረኝ ይሻለኝ ነበር..። የሆነ ክፉ ነገር እንዳሰበች ተረዳሁ። በቃ ልትለየኝ ነው ስል ብዙ ስጋት ሰጋሁ። አፌ አያቴን ሊረግም አሞጠሞጠ..ግን በአያቴ ላይ አልደፈረም።

ከዚህ ንግግር በኋላ ለሶስት ቀን አናወራም.. አንነጋገርም። በጣም ስለማፈቅራት ሁሌ የምለማመጣት እኔ ነኝ። ትዝታን አጥቼ መኖር አይደለም መሰንበት የምችል አይመስለኝም። ለዛም ነው የተኮራረፍንባት ሶስት ቀን ዝንታለም የምትሆንብኝ። ህይወቴን በውብ ቀለም ቀልማ አምሬ እንድታይ ያደረገችኝ እሷ ናት። ፍቅሯ አሸክታቤ ነው.. እሷ ደግሞ ጥቁር መላዕኬ። አያቴን ባስተዋውቃት ከእሷ ይልቅ እኔ ነበርኩ የምደሰተው ግን አያቴን ፈራኋት..ጥቁር መልክ አትወድም። ጥቁር ሰው አይሆነንም፣ ጥቁር ሰው ገፊያችን ነው እያለች ነው ያሳደገችኝ። ያ ሲያየኝ ጭራውን እየቆለ እግሬ ላይ የሚንደባለለውን የጎረቤታችንን ጥቁር ውሻ እንኳን ብዙ ጊዜ ወርውራ ስታው እንዳላየው ስትል በመርዝ ያስገደለችው እሷ ናት። ጥቁር ስለሆኑ ብቻ ከብዙ የልጅነት ጓደኞቼ ተቆራርጫለው። ትዝታ ደግሞ ጥቁር ናት..ድብን ያለች ጥቁር። ይቺን ሴት አያቴ ፊት ባቀርባት አያቴ ምን ልትሆን እንደምትችል ሳስብ እሰቃያለው። አያቴ ስትናገር ሰው ይከፋዋል አትልም፣ የመጣላትን ነው የምትተፋው። ኋላ አስቀይማት ስል እሰጋለው..

ትዝታ እንደእስከዛሬው በቀላሉ አልታረቀችኝም.. መህላዋን የምፈራው ለዚህ ነው። ‹ውሸታምና ቃለአባይ ሰው ፍቅረኛዬ እንዲሆን አልፈቅድም። ከእንግዲህ ከአንተ ጋር ነገ አይኖረኝም። ለሁሉም ነገር አንድ ሳምንት እሰጥሀለው። ስትል በአፏ ልትነግረኝ ተጸይፋኝ በማውቀው ጠማማ የእጅ ጽሁፏ ወረቀት ላይ ጽፋ ጠረጴዛው ላይ ትታልኝ እብስ አለች። ትዝታ እንዴት መውደድ እንደሚቻል የማወቋን ያክል እንዴት እንደሚጠላም ታውቃለች።

ምንም ሳልሰራበት የሰጠችኝ የጊዜ ገደብ ሊጠናቀቅ አራት ቀን ቀረው። ሶስቱን ቀን ጥቁር አምልኮዋን ከተወች ብዬ አያቴ ፊት አሳዛኝ ፊቴን ይዤ ስንጎራደድ ሰነበትኩ። እሷ ግን ምንም ያው ናት። በቴሌቪዥን ያየችውን ጥቁር ሰው እየተጸየፈች ‹ኧረ ዝጋው ወዲያ! ምኑን ነው የሚያሳየኝ..የሰው ዲያቢሎስ› ትለኛለች። ፊቷን በቴሌቪዥን ከሚታያት ጥቁር ሰው እያሸሸች። አያቴ ፊት ስለትዝታ ለማንሳት አቅም አጣሁ። ሳምንቱ አለቀ። ነፍሴን ያራቆቱ ሰባት ቀናቶችን ተጋፈጥኩ። ትዝታ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ረሳችኝ። ሳምንቱ ለወር ሲቀርብ..ብቻዬን ማውራት ጀመርኩ። በፍቅሯ ላብድ ትንሽ በቀረኝ አንድ ማለዳ ላይ አያቴን ‹የምትወጂኝ ከሆነ ወደ አንድ ቦታ አብረሽኝ እንድትሄጂ እፈልጋለው..እንቢ የምትይኝ ከሆነ ግን ተመልሼ ቤትሽ አልመጣም› አልኳት። እግዜር ይስጣት እሺ አለችኝ..አያቴን የከቷን አልብሼ ጥቁሯ ፍቅረኛዬ ትዝታ ፊት ሳቆማት የሆነችውን መሆን መቼም አልረሳውም።

ከትዝታ በኋላ አያቴ ከጥቁር ውጪ የምትወደው ቀለም ጠፋ። ትዝታ የአያቴን የአጉል እምነት አይነጥላ ገፋ ለእኔ ሚስት ለአያቴ ደግሞ የማትተካ ምራት ሆነች።

# ዓለም አቀፍ



## የአይ ኤስ መሪው አቡ አል ሐሰን አል ሃሽሚ አል ቁራይሺን መገደሉ ተነገረ

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- አቡ አል ሐሰን አል ሃሽሚ አል ቁራይሺን በአውደ ውጊያ መገደሉን የአይ ኤስ ቡድን ቃለ አቀባይ አቡ አል ሙሃጂር በለቀቀው አጭር የቪዲዮ ይፋ ማድረጉን ቢቢሲ ዘገበ።

በወጣ የድምፅ መልዕክት መሪው የተገደለው "የአምላክ ጠላቶች" በሚል የጠራቸውን ሲዋጋ ነው ቢልም አሜሪካ በበኩሏ መሪው የተገደለው አማጺው በሶሪያ ነጻ ጦር ጥቅምት አጋማሽ ላይ በደቡብ ምዕራብ ሶሪያ ባካሄደው ዘመቻ መሆኑን አስታውቃለች። የቡድኑ ተተኪው መሪ ቃለ አቀባዩ አል- ሁሴን አል ሁሴይኒ አል ቁራይሺ የሚባል እንደሆነ ገልጿል።

አቡ አል ሑሴይንን "ከአንጋፋዎቹ ጂሃዲስቶች አንዱ"በማለት ያሞካሸው ቃል አቀባዩ የቡድኑ ደጋፊዎች ታማኝነታቸውን እንዲያሳዩም ጠይቋል።

ነገር ግን እንደ ከዚህ ቀደሙም ቃል አቀባዩ የአዲሱን መሪ ትክክለኛ ስሙን፣ ዜግነቱን እንዲሁም ታሪኩን ከመግለጽ ተቆጥቧል።

አቡ አል ሀሰን አሜሪካ በየካቲት ወር 2022 የቀድሞውን የአይ ኤስ መሪ አቡ ኢብራሂም አል ሀሽሚን በሶሪያ መግደሏን ካሳወቀች በኋላ ቡድኑን መምራት መጀመሩ ይነገራል።

ስለ አቡ አልሐሰን ብዙም የሚታወቅ ነገር የለም፤ መሪም ከሆነ በኋላም በስሙ መግለጫ አውጥቶ የማያውቅ ሲሆን አሜሪካ በግድያው ተሳትፎ እንዳላደረገችና እስካሁን ለግድያው ኃላፊነቱን የወሰደ የለም።

የአሜሪካ የብሄራዊ ደህንነት ምክር ቤት ቃል ጆን ኪርቢ ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ፥ የአይ ኤስ መሪዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ እየተወገዱ መሆኑ ለፀረ ሽብር እንቅስቃሴው ኃይል ይጨምራል ነው ያሉት።

የቡድኑን ታጣቂዎች በግድያ በመመናመናቸው አዳዲስ አባላትን ለመመልመል በማህበራዊ ሚዲያዎች ዘመቻ ላይ ሲሆኑ በሌላ በኩል ደግሞ መሪዎቹ እየተገደሉ አሁንም በሶሪያና ኢራቅ የሽብር ጥቃት መቀጠሉ ተገልጿል።



## በቦኩሃራም ታግተው የነበሩ የናይጄሪያ ልጃገረዶች ጽንስ ማቋረጥ ተከለከሉ

በጋዜጣዉ ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡ በአሸባሪው ቦኩሃራም ቡድን ከታገቱ በኋላ ያመለጡት የቺቦክ ናይጀሪያ ልጃገረዶች እርጉዝ ሲሆኑ ጽንሱን ለማቋረጥ የአገሪቱ ጤና ተቋማት ፍቃደኛ አለመሆናቸውን አልአፍሪካ ድህረ ገጽ ዘገበ።

በቡድኑ ከትምህርት ገበታቸው ከታገቱት ልጃገረዶች 13 ማምለጥ ቢችሉም ሁሉም እርጉዝ ሆነው ተገኝተዋል። ልጃገረዶቹ በአሁኑ ጊዜ መንግሥት ባዘጋጀላቸው የማቆያ ማዕከል የተገኙ ሲሆን መንግሥት ወደ ትምህርት ገበታቸውና ወደ ቤተሰባቸው እንዲመልስ ለቦርኖ ግዛትና ለፌዴራል ባለሥልናት ያቀረቡት ተደጋጋሚ ጥያቄ እስካሁን መልስ እንዳልተሰጣቸው ተነግሯል።

ልጃገረዶቹ የጠዋቱ ህልማቸው እውን እንዲሆንላቸው መንግሥት ከቻለ ለሌሎቹ እድል እንደሰጠ ሁሉ ወደ ውጭ አገር ልኳቸው እንዲያስተምራቸው የገለጹ ሲሆኑ፤ ካልቻለ ደግሞ ወደ ቤተሰባቸው መልሶአቸው ትምህርታቸውን መከታተል እንዲችሉ ሁኔታ እንዲያመቻችላቸው ጠይቀዋል።

በቦኩሃራም የታገቱት ሁሉም የቺቦክ ልጃገረዶች እርጉዝ በመሆናቸው ለከፍተኛ የሥነልቦና ቀውስ ተዳርገዋል። በመሆኑም አብዛኞቹ ጽንስ የማቋረጥ ፍላጎት እንዳለቸው ተገልጿል። በአንጻሩ የናይጀሪያ ተቋማት ከአገሪቱ ባህል ባፈነገጠ መልኩ ውርጃን የማበረታታት ሥራ እንደማይሰሩ በተደጋጋሚ ሲናገሩ ይደመጣሉ።

መንግሥት ቤተሰባቸውን እንዲጎበኙ መፍቀዱን ያመሰገኑት እነዚህ ልጃገረዶች፤ ነገር ግን ጎብኝቱ ብቻውን ችግራቸውን ስለማይፈታላቸው ወደ ቤተሰባቸው ተመልሰው ትምህርታቸውን መከታተል እንዲችሉ እንዲፈቅድላቸው እና ለሚወልዱት ሕጻናትም ተገቢውን እንክብካቤ እንዲያደርግ ጠይቀዋል።

# ነፃ ሃሳብ

## የፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት እና መሰረታዊ ነጥቦቹ

እስማኤል አረቦ

ለሁለት ዓመታት ያህል በመንግስትና በሕወሓት መካከል ሲደረግ የነበረው ጦርነት ጥቅምት 23 ቀን 2015 በፕሪቶሪያ በተካሄደው የሰላም ስምምነት ህገ መንግስታዊ ስርዓቱን መሰረት አድርጎ ሉዓላዊነትንና የግዛት አንድነትን እና ብሔራዊ ጥቅምን ባከበረ መልኩ ዕልባት አግኝቷል። የተደረሰው ስምምነት ደም አፋሳሹን ጦርነት ለማስቆም፣ ዕርዳታ እና መሠረታዊ አገልግሎቶች ለማስጀመርና የአገሪቱን የድንበርና የግዛት አንድነት እንዲሁም ሕገ መንግስታዊ ስርዓት እንዲከበር የማድረግ ዓላማ አለው።

በአጠቃላይ ሲታይ በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ የተፈረመው የሰላም ስምምነት እንዲሁም ይህንን ተከትሎ በኬንያ ናይሮቢ የተፈረመው ባለ 12 ነጥብ የማስፈጸሚያ ሰነድ የሚከተሉትን መሰረታዊ ነጥቦች የያዘ ነው።

### ህገ መንግስታዊ ስርዓትን ማጽናት

ህገ መንግስታዊ ስርዓቱ ከኢፌዴሪ ህገ መንግስት የሚመነጭ ነው። በህገ መንግስቱ አንቀጽ 102 በፌዴራልና በክልል የምርጫ ክልሎች ነጻና ትክክለኛ ምርጫ በገለልተኝነት እንዲካሄድ የማድረግ ስልጣን ያለው የምርጫ ቦርድ እንደሆነ በግልጽ ተደንግጓል። ሆኖም ከዚህ ድንጋጌ በተቃረነ መልኩ በትግራይ ክልል «ምርጫ» ተካሂዷል በሚል የትግራይ መንግስት መቋቋሙን ስሁት በሆነ መልኩ ለማወጅ መሞከሩ የሚታወስ ነው። በወቅቱም የኢትዮጵያ መንግስት በትግራይ የተካሄደውን «ምርጫ» እንዳልተካሄደ የሚቆጠር፤ በመግለጽ ተቀባይነት እንደሌለው አስታውቆ ነበር።

ይህንኑ ሃሳብ የሚያጸና ውሳኔ በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ በተካሄደው ስምምነትም ስፍሮ እናገኘዋለን። ምርጫው ህገ ወጥ በመሆኑም በትግራይ የሽግግር መንግስት ይቋቋማል፤ በሂደትም ምርጫ ተካሂዶ ክልሉን የሚያስተዳድር መንግስት ይጸናል። ስለሆነም አሁን ባለው ሁኔታ የትግራይ ህዝብን ሰላም የሚያስጠበቅውና ህጋዊ ውክልና ያለውም የፌዴራል መንግስት ብቻ ነው። ከዚህ ውጭ በትግራይ ህዝብ ተመርጫለሁ የሚል ህጋዊ አካል የለም። ስለሆነም ከዚህ ውጭ የሚቀርቡ ጉዳዮች በፕሪቶሪያው ስምምነት መሰረት ተቀባይነት የላቸውም፤ በዚህ ጉዳይ ሊቀመጥ የሚችል ቅድመ ሁኔታም የለም።

በሌላ በኩል የፕሪቶሪያው ስምምነት በግልጽ ካስቀመጣቸው ነጥቦች ውስጥ ሌላኛው በአንድ አገር ውስጥ አንድ መከላከያ ሰራዊት ብቻ መኖር አለበት የሚለው ነጥብ ነው። በስምምነቱ ላይ ዋነኛ ጉዳይ የሆነውን ትጥቅ ማስፈታትን በተመለከተ ሁለቱም ወገኖች በኢትዮጵያ ውስጥ አንድ የመከላከያ ኃይል ብቻ እንዳለ ከስምምነት ደርሰዋል።

ስለዚህም ከተለያዩ አካላት የሚወጡ መረጃዎች እንደሚያመላክቱት ትጥቅ የማስፈታቱን ሂደት በጥሩ ሁኔታ ለማስኬድ እየተሰራ ይገኛል። ይህንን ሁኔታ የተለያዩ ቅድመ ሁኔታዎችን በማስቀመጥ ለማጓተት መሞከር አይችልም። በፕሪቶሪያው ስምምነትም ሆነ በናይሮቢው የማስፈጸሚያ ሰነድ መሰረት ስምነቱን ወደ ተግባር ከመለወጥ ውጭ ሊቀመጥ የሚገባ ቅድመ ሁኔታ አይኖርም።

ሌላው በፕሪቶሪያው ስምምነት የፌዴራል መንግስትና ሕወሓት ውሳኔ ካሳለፉባቸው ጉዳዮች መካከል የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነትን የማስጠበቅ ስልጣን የኢትዮጵያ መንግስት ብቻ እንደሆነ በውል ሰፍሯል። በተለይም ከውጭው ዓለም ጋር የሚደረጉ ግንኙነቶችና ስምምነቶች ሁሉ ሊከናወኑ የሚችሉት በፌዴራል መንግስት ብቻ መሆኑ ከስምምነት ላይ የተደረሰበት ነጥብ ነው። ይህው ሃሳብም በህገ መንግስቱ አንቀጽ 51 ንኡስ አንቀጽ 8 ላይ በግልጽ ሰፍሮ ይገኛል።

በአጠቃላይ የፕሪቶሪያው ስምምነት የኢትዮጵያን ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት የሚያጸናና የዜጎችን ሰቆቃ የሚቀርፍ ስምምነት በመሆኑ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ የሚተገበር ነው። ስምምነቱ የኢትዮጵያን አንድነትና ሉዓላዊነት ከማጽናቱም ባሻገር በጦርነት ሰቆቃ ውስጥ የነበሩትን የትግራይ፤ የአማራና የአፋር ህዝቦችን እፎይታ አጎናጽፏል።

ከፕሪቶሪያው ስምምነት ቀጥሎ የተካሄደው የናይሮቢ ስምምነት መተማመንን የፈጠረና ኢትዮጵያ የጀመረችውን የሰላም መንገድ የሚያጸና ነው። በተለይም በጦርነቱ ምክንያት የተቋረጡ መሰረተ ልማቶችንና ሰብዓዊ ድጋፎችን በሚፈለገው መልኩ ለማድረስ መሰረት የጣለ ነው። በዚሁ መሰረትም በትግራይና በአማራ ክልሎች አንዳንድ አካባቢዎች ተቋርጠው የነበሩ የቴሌኮሙኒኬሽን፤ የኤሌክትሪክና የባንክ አገልግሎቶች መልሰው ወደ አገልግሎት እንዲገቡ ለማድረግ አስችሏል። የሕዝቡን ችግር በፍጥነት ለመቅረፍም ሥራዎች በስፋት እየተሰሩም ይገኛሉ።

የፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት ምንም አይነት ቅድመ ሁኔታ እንደሌለውና በስምምነቱ መሠረት እንደሚፈፀምም የኢፌዴሪ የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዶክተር ለገሰ ቱሉ መግለጻቸውም የሚታወቅ ነው።

በአጠቃላይ ለአገር ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነት መሰረት የሆነውና የዜጎች ሰቆቃ እንዲበቃ ያደረገው የፕሪቶሪያው ስምምነት ቅድመ ሁኔታ የለውም፤ ስለሆነም በስምምነቱ መሠረት መፈጸም ከሁሉም ወገን የሚጠበቅ ግዴታ ነው። ያለውም ብቸኛው አማራጭ ይሄው ብቻ ነው!

### ግጭትን በዘላቂነት ማስቆም

የኢትዮጵያ መንግስትና ሕወሓት በደቡብ አፍሪካ ለ10 ቀናት ከመከሩ በኋላ በዘላቂ ግጭት ለማቆም ተስማምተዋል። ባለፉት ሁለት አመታትም የኢትዮጵያ ህዝብ የአገር ሉዓላዊነትና የግዛት አንድነትን ለማረጋገጥ በርካታ መስዋዕትነት የከፈለ ህዝብ ነው።በመስዋዕትነቱም የአገሩን ሉዓላዊነት አጽንቷል፤ አንድነቱን አጠናክሯል፤ ዳር ድንበር አስከብሯል። የኢትዮጵያን መፍረስ ለሚመኙ ባዕዳን በቂ ትምህርት ሰጥቷል።

የኢትዮጵያ ህዝብና መንግስት ወደማይፈልጉት ጦርነት ከመግባታቸው በፊት በርካታ የሰላም ጥረቶችን ሲያደርጉ ቆይተዋል። ሽማግሌዎችንና ታዋቂ ሰዎችን ጭምር በመላክ ለሰላም ያላቸውን ፍላጎት በተደጋጋሚ ገልጸዋል። ከዚህም አልፎ ኢትዮጵያ አውዳሚው ጦርነት ውስጥ ሆና የሰላም ያለህ ሲሉ ቆይተዋል። ለሰላም ሲባል ስትል የትም ቦታ፤ በማንኛውም ጊዜ እና በማንኛውም ርዕሰ ጉዳይ ለመወያየት ፍቃደኝነታቸውን ገልጸዋል። ጥረቱም ፍሬ አፍርቶ በመንግስትና በሕወሓት መካከል ታሪካዊ የሚባል የሰላም ስምምነት ተፈርሟል።

በአፍሪካ ህብረት ጥላ ስር በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ በተካሄደው የሰላም ስምምነት ሁለቱም ወገኖች ታሪክ ጽፈዋል። አስራ ሁለት አንቀጽ ያለው የሰላም ስምምነት በማውጣት ሰላምን አውጀዋል። በፕሪቶሪያ የተካሄደው ስምምነት ለዘመናት መፍትሄን በጠብመንጃ ለማምጣት ሲኬድበት የነበረውን ኋላ ቀር አስተሳሰብ የሰበረና ስልጡን የሆነ አካሄድን ለአገራችን ያስተዋወቀ ነው። ስምምነቱ የኢትዮጵያን መሰረት ከማጽናቱም ባሻገር በጦርነት ሰቆቃ ውስጥ የነበሩትን የትግራይ፤ የአማራና የአፋር ህዝቦችን እፎይታ አጎናጽፏል።

"በዘላቂነት የጦር መሳሪያ ድምጽ እንዳይሰማ ለማድረግ እና በሰሜን ኢትዮጵያ ለሁለት ዓመት የዘለቀው ግጭት እንዲቆም ተስማምተናል" ብለዋል ሁለቱ አካላት።

ሕወሓት እና መንግሥት በአንድ ድምጽ ግጭቱ ከፍተኛ ሰብዓዊ እና ቁሳዊ ኪሰራዎችን አስከትሏል ካሉ በኋላ፤ የኢትዮጵያን ሕዝብ ጥቅም ከግምት በማስገባት ግጭቱን ምዕራፍ ከኋላችን ትተን "በሰላም እና በመቻቻል ለመኖር" ተስማምተናል ብለዋል።

### ትጥቅ ማስፈታት

የኢትዮጵን ሉዓላዊነት እና የግዛት አንድነት ማረጋገጥ እና መጠበቅ መሠረታዊ ጉዳይ ነው ያሉት ሕወሓት እና ኢትዮጵያ መንግሥት፤ የኢፌዴሪ ሕገ-መንግሥትን ለማስከበር ተስማምተዋል።

በስምምነታቸው መሠረት 'ኢትዮጵያ አንድ የአገር መከላከያ ሠራዊት ብቻ ነው ያላት' በሚለው ጉዳይ ተስማምተዋል። በስምምነቱ ላይ የሕወሓት ኃይሎች "ከቀላል ጦር መሳሪያዎች" ጀምሮ በ30 ቀናት ውስጥ ትጥቃቸውን ይፈታሉ።

የኢትዮጵያ ፌደራል የፀጥታ ኃይሎች "በትግራይ ክልል ውስጥ የሚገኙትን ሁሉንም የፌደራሉን ተቋማትና አየር ማረፊያዎችንና አውራ ጎዳናዎችን ጨምሮ ዋነኛ መሠረተ ልማቶችን" ሙሉ ለሙሉ እንደሚቆጣጠሩ ተጠቅሷል።

"መሬት ላይ ያለውን የጸጥታ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት የሕወሓት ተዋጊዎች ትጥቅ የሚፈቱበት፣ የሚበተኑበት እና ወደ ማሕበረሰቡ ተመልሰው የሚቀላቀሉበት ዝርዝር ፕሮግራም ላይ ተስማምተናል" ብለዋል። ይህም በአሁኑ ወቅት በተለያየ ደረጃ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን እየተገለጸ ነው። እስከ ኅዳር 24 ቀን 2015 ድረስ ሕወሓት ከባድ መሳሪያዎችን እንደሚፈታና አነስተኛ መሳሪያዎችን በሂደት የማስፈታቱ ሂደት እንደሚቀጥል በኬንያ የኢትዮጵያ አምባሳደር ባጫ ደበሌ ተናግረዋል።

### የሰብዓዊ እርዳታ አቅርቦት

የኢትዮጵያ መንግሥት ከሰብዓዊ ድርጅቶች ጋር በመሆን የሰብዓዊ እርዳታ ለሚያስፈልጋቸው የተፋጠነ እርዳታ እንዲያደርስ ከመግባባት ላይ ተደርሷል።

ካለፈው ሳምንት ጀምሮ ሰብዓዊ ድጋፍ የጫኑ 67 ተሽከርካሪዎች ወደ ትግራይ ተጉዘዋል። ተሽከርካሪዎቹ ወደ ሽሬ፣ ሽራሮና አክሱም ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ድጋፎችን ማዳረስ ጀምረዋል። ከ67 ተሽከርካሪዎች መካከልም መድኃኒትና የህክምና ቁሳቁስን የያዘ ተሽከርካሪም መካተታቸውን መረጃዎች ያሳያሉ።

ዓለም አቀፉ የቀይ መስቀል ማህበርም ወደ ሽሬ የሙከራ በረራ ማድረጉንና ርዳታ በአየርም በየብስም ለማድረስ እየሰራ መሆኑን መግለጹ አይዘነጋም። ካሳለፍነው ሳምንት ጀምሮም ማህበሩ በትግራይ በዘጠኝ የህክምና ተቋማት መድሃኒቶችንና አስቸኳይ ዕርዳታዎችን በማከፋፋል ላይ ይገኛል። ዩኑሴፍም ከስምምነቱ ወዲህ ዛሬ ወደ ትግራይ የመጀመሪያው ሕይወት አድን ድጋፍ በተለይም ለህፃናት እና ሴቶች አስገብቷል። እስከ ትላንትና በስቲያ ድረስ ሰብዓዊ ዕርዳታ የጫኑ 317 መኪኖች ወደ ትግራይ ገብተው ለህብረተሰቡ ድጋፍ በማድረግ ላይ ናቸው።

በተመሳሳይም መንግስት አስቸኳይ ሰብዓዊ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ዜጎች ለመድረስ ከዓለም አቀፍ የልማት አጋሮች ጋር በመተባበር በሶስት አቅጣጫ (ኮሪደር) ወደ ትግራይ ክልል የሰብዓዊ ድጋፍ እያጓጓዘ መሆኑን የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አስታውቋል።

በኢትዮጵያ ፌደራል መንግስትና በሕወሓት መካከል በፕሪቶሪያ የተደረሰውን ስምምነት ተከትሎ መንግስት ቃል የገባውን በትግራይ የሰብዓዊ ድጋፍ አቅርቦትና የመልሶ ግንባታ ስራዎችን እያከናወነም ይገኛል። ባለፉት አራት ቀናትም ዋና ዋና የሰብዓዊ ድጋፍ በተለያየ አቅጣጫ እያቀረበ እንደሚገኝም ነው የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት የገለጸው።

በዚህም በጎንደር ኮሪደር ሕዳር 17- ከጎንደር በሁመራ በኩል ወደ ሽሬ 1 ሺህ 137 ሜትሪክ ቶን የምግብ እህል የጫኑ 30 የዓለም ምግብ ፕሮግራም የጭነት መኪኖች የተላኩ ሲሆን፥ በተጨማሪም 212 ሜትሪክ ቶን እህል የጫኑ 10 የጭነት መኪኖች ከጎንደር ወደ ማይፀብሪ መጓዛቸውንም አስታወቋል።

ከዚህ ባለፈም ኅዳር 18 ቀን የዓለም ምግብ ፕሮግራም በ24 መኪኖች 1 ሺህ 43 ሜትሪክ ቶን የምግብ እህል ከጎንደር ወደ ሽሬ ሲላክ፥ ኅዳር 19 ቀን ከሽሬ ወደ ማይፀብሪ የእርዳታ እህል የሚያጓጉዙ 11 ከባድ ተሽከርካሪዎች እየተጫኑ መሆኑንም ገልጿል።

ኅዳር 20 ቀን 380 ሜትሪክ ቶን የምግብ ድጋፍ የጫኑ 17 የዓለም ምግብ ፕሮግራም የጭነት መኪኖች ከጎንደር ወደ ማይፀብሪ (ዲማ) መላካቸውን በመጥቀስም፥ ከጎንደር ወደ ሽሬ የምግብ ድጋፍ ያደረሱ 9 የጭነት ተሽከርካሪዎች ወደ ጎንደር ተምለሰዋልም ነው ያለው።

እንዲሁም በኮምቦልቻ ኮሪደር ኅዳር 17 ቀን ከኮምቦልቻ የተነሱ 626 ሜትሪክ ቶን የምግብ ድጋፍን የጫኑ 22 የጭነት ተሽከርካሪዎች ዛታ የደረሱ ሲሆን፥ ኅዳር 18 ቀን የዓለም ምግብ ድርጅት 54 የምግብ እህል የጫኑ ተሽከርካሪዎች ከኮምቦልቻ ተነስተው ወደ ኦፍላ፤ ራያ አላማጣ መድረሳቸውም ተገልጿል።

ኅዳር 19 ቀን በደቡባዊ ዞን ውስጥ ለሚገኙት ባላ፣ ኮረምና ሌሎችም ወረዳዎች የሚላክ የምግብ እህል ጭነት እየተካሄደ መሆኑንም ነው አገልግሎቱ የጠቀሰው። በሰመራ ኮሪደርም ኅዳር 17 ቀን 34 የተለያየ ድጋፍ የጫኑ ተሽከርካሪዎች መቐለ የደረሱ ሲሆን፥ 77 ሜትሪክ ቶን ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁስ፣ 1 ሺህ 223 ሜትሪክ ቶን የምግብ እህል እንዲሁም 95 ሺህ 272 ሊትር ነዳጅ መቐለ ደርሰዋል ብሏል።

ኅዳር 18 ቀን በካቶሊክ ሪሊፍ ሰርቪስ በኩል የተላኩ በድምሩ 175 መኪኖች መቐለ ሲደርሱ፥ ኅዳር 20 ቀን የምግብ ድጋፍ የጫኑ 140 ተሽከርካሪዎች ከሰመራ ወደ መቐለ ጉዞ መጀመራቸውንም ነው ያስታወቀው።

ከዚህ በተጨማሪም ኅዳር 20 ቀን በተባበሩት መንግስታት ድርጅት የሰብዓዊ የአየር በረራ አገልግሎት በኩል ከአዲስ አበባ ወደ መቐለ የመንገደኞች የአውሮፕላን በረራ መከናወኑንም በመግለጫው አመላክቷል።

በአጠቃላይ በኢትዮጵያ መንግስትና በሕወሓት መካከል የተደረሰውን የሰላም ስምምነት ተከትሎ በተለይ በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል በግጭት የተጎዱ የትግራይ፣ አማራና አፋር አካባቢዎች የሰብዓዊ ድጋፍ እንዲደርስ በማድረግ ረገድ በመንግስትና በሰብዓዊ ድጋፍ ሰጪ አካላት ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት በመከናወን ላይ ይገኛል።

መንግስት የፕሪቶሪያውን የሰላም ስምምነት መሰረት በማድረግ የሚጠበቅበትን ሃላፊነት በተሟላ መልኩ እየተወጣ ነው። አቅም በፈቀደና አጋር አካላት ማቅረብ በቻሉት መጠን የሰብዓዊ እርዳታና መድሃኒት በሁሉም አቅጣጫ ወደ ትግራይ ክልል እንዲገባ እያደረገ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ።

### የተቋረጡ መሰረተ ልማቶችን መልሶ መገንባት

በፕሪቶሪያው ስምምነትም ሆነ ቀጥሎ የተካሄደው የናይሮቢ ስምምነት መተማመንን የፈጠረና ኢትዮጵያ የጀመረችውን የሰላም መንገድ የሚያጸና ነው። በተለይም በጦርነቱ ምክንያት የተቋረጡ መሰረተ ልማቶችንና ሰብዓዊ ድጋፎችን በሚፈለገው መልኩ ለማድረስ መሰረት የጣለ ነው። በዚሁ መሰረትም በትግራይና በአማራ ክልሎች ተቋርጠው የነበሩ የቴሌኮሙኒኬሽን፤ የኤሌክትሪክና የባንክ አገልግሎቶች መልሰው ወደ አገልግሎት እንዲገቡ ለማድረግ ተችሏል።

በአጠቃላይ ሕወሓት በሕገ መንግሥቱ መሰረት የተቋቋሙ የፌደራል ተቋማትን አክብሮ ለመንቀሳቀስ የተስማማ ሲሆን፣ ይህም የፌደራል መንግሥቱ የፌደራል ተቋማትን ንብረት፣ የአገሪቱን ዓለም አቀፍ ድንበርን የመጠበቅ ኃላፊነት የመንግሥት ይሆናል።

ሕወሓት በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል ውስጥ ታጥቀው የሚንቀሳቀሱ አማፂ ቡድኖችን ከመደገፍም ሆነ አብሮ ከመስራት ለመታቀብ ተስማምቷል። የፌደራል መንግሥቱ የአገር መከላከያ ሠራዊትን፣ የደኅንነት አካላትን እና ሕግ አስከባሪ አካላትን ሕገ መንግሥታዊ ግዴታቸውን እንዲወጡ ሲያስማራ አክብሮ ለመንቀሳቀስ ተስማምቷል።

ሕወሓት ለግጭት እና አመጽ የሚደረጉ ምልመላዎች፣ ሥልጠናዎች ወይም ዝግጅቶችን ከማድረግ ይታቀባል። ሕወሓት ያለ ፌደራል መንግሥቱ እውቅና ከማንኛውም የውጭ አካል ጋር ግንኙነት ማድረግ ያቆማል።

የፕሪቶሪያው ስምምነትም ሆነ በናይሮቢ የተፈረመው የማስፈጸሚያ ሰነድ የሰላም ስምምነቱ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱንና ብሔራዊ ጥቅማችንን ባስከበረ መልኩ የተፈጸመ ነው። ስምምነቱ ላይ መድረስ የተቻለውም የጸጥታ ኃይሎችና የደኅንነት ኃይሎች በከፈሉት መስዋዕትነትና ባስመዘገቡት ድል፣ ሕዝቡ በአንድ ላይ በመቆሙ እና መንግሥት ሰላምን ለማምጣት ባለው ቁርጠኝነት ነው።